**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።**

# የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ

## ምዕራፍ አንድ

## የቤተክርስቲያን ታሪክ መግቢያ

### የቤተክርስቲያን ትርጉም እና ስያሜ

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ከግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጓሜውም ማደር ፣ ወገን ነገድ፣ ዘር ጉባኤ ፣ ማኅበር ፣ ቤተሰብ ማለት ነው።

- ❖ ቤተክርስቲያ ለሚለው ቃል ሶስት ዋና ዋና ትርጉዎች በሃይማኖት ትምህርት ይሰጠዋል።
- ➢ በመጀመሪያ ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ማደሪያ ፣ የክርስቲያኖች ቤት የሚል ትርጉም በመስጠት ቤቱን መሰብሰቢያውን ሕንፃውን ያመለክታል። ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ፣ ስለበደላቸው ምህረት ለመለመን ፣ ሕይወት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በተለይም ደግሞ ለኃጢያት ሥርየት የተሰዋውን የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል የሚሰባሰቡበት ቤት ቤተክርስቲያን ተብሎ ይጠራል። ከጌታ ትንሳኤ በኋላ ደቀመዛሙርቱ በኢየሩሳሌም ከተማ የማርቆስን እናት የማርያምን ቤት እንደ ቤተክርስቲያን ይጠቀሙበት ነበር። የመጀመሪያዋ ሕንፃ ቤተክርስቲያን የተሰራችው በፊልጵስዩስ ከተማ ነው አሁን ግን በዓለም ሁሉ ታንፃለች።
- ➢ በሌላም በኩል ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል እያንዳንዱን ክርስቲያን ሊያመለክት ይችላል። ይህም “ቤተ” ማለት ወገንን በሚያመለክትበት ጊዜ ነው። ቤተ ያዕቆብ ቤተ ሌዊ ፣ ቤተ እስራኤል ወዘተ እንደሚባለው ሁሉ የክርስቶስ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ። በጥምቀትም የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ስጦታን ስለሚያገኙ የተቀደሱና የተከበሩ ናቸው። ዳግም ኃጢአትን ሠርተው ራሳቸውን እስካላደፋ ድረስ ንጹህ ማደሪያው ናቸውና ቤተክርስቲያን ይባላሉ።
- ➢ በመጨረሻም ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች አንድነት ጉባኤ ወይም ማኅበር ማለት ነው። ጌታ ስለይቅርታ ሲያስተምር “ወንድምህ ቢበድልህ ሔደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው … ባይሰማህ ግን አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ እነርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት ደግሞም ቤተክርስቲያንን ባይሰማት እንኳ እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁንልህ።” በማለት ገልጿል (ማቴ 18÷15-17) እዚህ ላይ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የክርስቲያኖችን ጉባኤ እንደሚያመለክት ግልጽ ነው።

“ቤተክርስቲያን” የሚለው ቃል በመጀመሪያ የተጠቀመበት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በቅዱስ ወንጌል እንመለከታለን (ማቴ 16÷18፣18÷18) ምእመናን (ደቀመዛሙርት) ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የተባሉት በአንፆኪያ ቢሆንም ቤተክርስቲያን የሚለው ስያሜ ቀድሞ በጌታችን የተሰጠን ስለሆነ አምላካዊ ስጦታችን ነውና እንጠብቀዋለን።

ቤተክርስቲያን በባህርይዋ አንዲት ብትሆንም ማንነቷን ለመግለጥና ለማስተዋወቅ እንዲሁም ከአገልግሎቷ አንፃር የተለያዩ መጠሪያዎች አሏት። ሐዋርያትም በዚሁ መንገድ በተለያየ ስም እንደጠሯት በአጭሩ እንመለከታለን።

- ✓ ቤተክርስቲያን ዘክርስቶስ (ዘእግዚአብሔር) ይህ ስያሜ የተሰጣት ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው የቤተክርስቲያን ራሷ ፣ ገዥዋ ፣አዳኟ ክርስቶስ ነው። ኤፌ 5÷1 ፣ ገላ1÷13 ፣ 1ተሰ 2÷14 ፣ 1ጢሞ 3÷5 ፣ 2ተሰ 1÷4
- ✓ ማኅደረ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ማደሪያ) እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑና በቸርነቱ ያድርበትና ሕዝቡን ይጎበኝበት ዘንድ በቤተክርስቲያን የሚገለጥና ፀጋውን የሚሰጥ በመሆኑ ኢሳ 36÷1 ፣ ኤፌ 2÷20-21 ፣ 1ቆሮ 13÷16
- ✓ መዝገበ ፀጋ (የፀጋው ግምጃ ቤት) ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ስጦታዎች የሚታደልበት ቦታ ስለሆነ ነው ዕብ 4÷16 ፣ 1ቆሮ 12÷11
- ✓ ቤተ ጸሎት (የጸሎት ቤት) ክርስቲያኖች ሁሉ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ፣ ምስጢራቸውንም ከእርሱ ጋር የሚወያዩባት ቤት ቤተክርስቲያን ናት። ኢሳ 56÷7 ፣ 2ዜና 7÷15-16
- ✓ ምስካዬ ኅዙናን (የነዳያን መጠጊያ) ቤተክርስቲያን የተቸገሩ ሁሉ የሚረዱባት ቤት በመሆኗ ሉቃ 16÷19÷31

## የቤተክርስቲያን ባሕርይ

### ❖ አንዲት ናት

ቅዱስ ጳውሎስ “ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሰራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።” “አንድ ጌታ ፣ አንድ ሃይማኖት ፣ አንዲት ጥምቀት ፣ አንድ አካልና አንድ መንፈስ” እያለ የገለጣት ቤተክርስቲያንን ነው። ምክንያቱም የቤተክርስቲያን ራስ አንድ ነው። እርሱም ክርስቶስ ነው። ኤፌ 4÷4-6 ሰዎች የተለያየ ሐሳብ ፣ የተለያየ ምኞትና ፈቃድ ሊኖራቸው ቢችልም ቤተክርስቲያን ግን የአንድ ክርስቶስ አካሉ ናትና አንዲት ናት።

- **ቅድስት ናት**

“እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ” ተብሎ ስለተጻፈ “የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ” (1ጴጥ 1÷15-16 በማለት የጌታ ደቀመዛሙርት ባስተማሩት መሠረት ቤተክርስቲያን የተቀደሰ ሥራ የሚሠራባት ፣ በውስጧም የሚገቡትና የሚኖሩት ሁሉ በየጊዜው ራሳቸውን የሚቀድሱባት ቤት ናት። ቤተክርስቲያን ቅዱስ በሆነው በክርስቶስ ደም የተቀደሰች ስለሆነች ቅድስት ናት። (የሐዋ 20÷28 1ቆቶ 6÷19)

- ❖ **ኩላዊት (የሁሉ) ናት**

ቤተክርስቲያን አንዲት ብትሆንም መንፈሳዊት ናትና በሁሉ ያለች የሁሉም ናት። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ግዑዛን ካላቸው ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነት ናትና በአንድ አካባቢ ብቻ ልትወሰን አትችልም ቤተክርስቲያን በሁሉ ያለች አምኖ ተጠምቶ በበሯ የሚገባውን ሁሉ ተቀብላ አካሏ የምታደርግ የሁሉም ናት እንጂ የተወሰነ ነገድ አይደለችም። (ኤፌ 1÷23)

- ❖ **ሐዋርያዊት ናት**

ቤተክርስቲያን መሠረቷ አንድ ጊዜ በክርስቶስ ተጥሏል ፣ ከዚያም በሐዋርያት ታንጿል ስለዚህ ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት ታስተምራለች ፣ እንደሐዋርያት ምስጢራትን ትፈፅማለች። ሐዋርያት የተቀበሉትንና የእነርሱ የሆነውን ቅዱስ ትውፊት ተቀብላ ትሰራበታለች እንጂ አዲስ ነገር ፈጥራ ራሷን ከግንዱ የምትለይ ቅርንጫፍ አትሆንም። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንኑ ሲያስረግጥ "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል" ብሏል ኤፌ 2÷20-21 እንደ ሐዋርያት የምታስምር እንደ እነርሱም የተለየ (ቅዱስ) ሰብስባ (ሲኖዶስ) ያላት ፣ በዚህም ሥርዓት የምትመራ በእነርሱ የሥርዓት መሠረት ላይ የታነፀች ስለሆነች ሐዋርያዊት ናት።

## የቤተክርስቲያን ታሪክ ምንጮች

- ❖ የቤተክርስቲያንን ታሪክ ስናጠና በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉን መጻሕፍት ፦
- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት
- በየጊዜው የተደረጉት የቤተክርስቲያን ጉባኤዎችና ውሳኔዎቻቸው
- የቤተክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው የታሪክ መጻሕፍት ፣ ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታና ጊዜ ተገኝተው የቤተክርስቲያንንና የዘመኑን ታሪክ የጻፉ ጸሐፊዎች /ሩፊያኖስ ፣ ሶቅራጥስ ፣ ዮሴፍ ወልደ ኦርዮን፣ አውሳብዮስ.../ የፃፏቸው መፃህፍት
- በየጊዜው የሚገኙት የክርስቲያኖች መቃብራት ፣ መቅደሶች ፣ ሥዕሎች ፣ ገንዘቦች ፣ የድንጋይ ላይና የብራና ጽሑፎች ፣ የአርኪዎሎጂ ጥናት ግኝቶች ወዘተ .... ለአስረጂነት ይጠቅማሉ።
- መንፈሳውያንም ሆኑ ዓለማውያን ነገስታት በቤተክርስቲያን ላይ የደነገጓቸው ልዩ ልዩ ህግጋት ወዘተ ታሪኮቿ ናቸው።

## የቤተክርስቲያን ታሪክ መማር ለምን ይጠቅማል?

- ✓ በሰው ልጅ አእምሮ የሚፈጠረውን ከየት መጣሁ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና የማወቅ ጉጉቱን ለማሟላት።
- ✓ ስላለፈው ዘመን ለማወቅ እና ከሚመጣው ፈተና ለመጠበቅ።
- ✓ ለእኛ ሲል ራሱን ለመስቀል አሳልፎ የሰጠልን የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የቤዛነት ሥራ እንደምን ተፈፀመ ብለን ይህንን በሚገባ ማስታወስ የምንችለውና ፍቅሩን የምንረዳው የቤተክርስቲያንን ታሪክ ስናውቅ ነው።

የቤተክርስቲያንን ታሪክ ማጥናት የአለም ታሪክ እንደማጥናት ነው። በሌላም በኩል የአለምን የታሪክ መዝግብት በባለቤትነት ይዛ በየዘመኑ የነበረውንም አሰናድታ ያቆየች ቤተክርስቲያን እንደመሆኗ መጠን የትኞቹ መዛግብት ለምን የት እንደሚገኙ ለመረዳት የቤተክርስቲያንን ታሪክ ማጥናት ያስፈልጋል።

## ምዕራፍ ሁለት

## አማናዊቷ የሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን

የቤተክርስቲያንን ታሪክ የሚያጠኑ ሊቃውንት የቤተክርስቲያንን ታሪክ በሶስት የተለያዩ ዘመናት ይከፍሉታል። ይኸውም፡ -

1. በዓለመ መላእክት (እስከአዳም መፈጠር ድረስ) የነበረችው የመላእክት አንድነት
2. ከአቤል ጀምሮ እስከ ሐዲስ ኪዳን መግቢያ (ማለትም እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዮሐንስ አባት እስከ ዘካርያስ) ድረስ ያለው የደጋግ ሰዎች አንድነት
3. በክርስቶስ ደም የተመሰረተችው የክርስቲያኖች አንድነት

- በዓለመ መላእክት የነበረውን የመላእክት አንድነት ስንመለከት የእግዚአብሔርን የምህረት፣ የቁጣ ወይም የማስጠንቀቂያ መልእክት ወደ ሰው ፣ የሰውንም ልመና ወደ እግዚአብሔር በማድረስ ያገለግላሉ። በአምልኮት ፣ በስብሐተ እግዚአብሔር ይህን በመሳሰለው ሁሉ አንድ በመሆናቸው ይህ አንድነታቸው ወይም ኅብረታቸው

ቤተክርስቲያን ይባላል፡፡

- እግዚአብሔር አዳም ንስሀ በገባ ጊዜ የሰጠውን የተስፋ ቃል በማሰብ የሰው ዘር ፈፅሞ እንዳይጠፋ በየወቅቱ ለበረከት የሚሆኑ አንዳንድ ሰዎች አትርፏል፡፡ከአዳም ጀምሮ እስከ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ ያሉት ህዝቡን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲመላለስ ሲመክሩና ሲያስተምሩ ሲገስጹም የቆዩ አባቶች ያደረጓቸው ድንቅ ተዓምራት እና ሥራዎቻቸው ሁሉ ከክርስቶስ ልደት በፊት የክርስቲያኖችን አንድነትና ህብረት ጠብቆ ያቆየ ነበር፡፡

## የአማናዊቷ ቤተክርስቲያን መመስረት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አንተ ጴጥሮስ ነህ ፣ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያን እሰራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም" (ማቴ 16÷18) በማለት እንደገለፀው አማናዊቷን ቤተክርስቲያን በእለተ ዓርብ በደሙ መሠረታት፡፡ ሐዋ 10÷28 በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ከተነሳ በኋላ ለ40 ቀናት እየተገለጠ ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተምራቸው ፣ ምስጢር ሲገልጥላቸውና ሲያጽናናቸው ከቆየ በኋላ በ40ኛው ቀን በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ ባረገ በ10ኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሳ በ50ኛው ቀን በኢየሩሳሌም ከተማ፣ በጽርሐ ጽዮን በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ተሰብስበው ሲጸልዩ ለደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው፡፡ በእሳት ላንቃ አምሳልም በእያንዳንዳቸው ራስ ላይም ይታይ ነበር፡፡ ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ፍሩሀን የነበሩት ጥቡዓን ደካሞች የነበሩት ብርቱዎች ሆነው በመንፈስ ታድሰው የቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮ በዚህ ዕለት ጀምሩ፡፡ሃምሳኛው ዕለት አይሁድ የእሸት በዓል (በዓለ ሰዊት) የሚያከብሩበት ቀን ነበርና ሐዋርያት ቋንቋ ተገልጦላቸው በአደባባይ ለእያንዳንዱ ሰው በየተወለደበት ቋንቋ የክርስቶስን ወንጌል ሰበኩ፡፡ በዚሁ ዕለት ብቻ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት 3ሺህ አይሁድ አምነው በመጠመቅ የቤተክርስቲያንን አንድነት ተቀላቀሉ፡፡ ስለዚህም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይህችን ዕለት "የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ፣ ቅዳሴ ቤት" በማለት ሰይመዋታል፡፡

## ለክርስትና እምነት መስፋፋት ምክንያቶቹ

ለአማናዊቷ ቤተክርስቲያን መመስረትና የክርስትና እምነት መስፋፋት ጥቂቶቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) ብሉይ ኪዳን እስክንድርያ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከዕብራይስጥ ህዝቡ ወደሚሰማው ወደ ግሪክ ቋንቋ ስለተተረጎመ ከአሕዛብ ብዙዎች በእግዚአብሔር አመኑ:: ቀጥሎም ነቢያት አስቀድመው ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ትንቢት የተናገሩለት ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ በእርሱ በማመን ክርስትናን ተቀበሉ፡፡

ለ) የሮም መንግስት ዓለሙን መግዛቱ ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ሰፊው የሮም ግዛት እንደዛሬው በየመንግስታቱ ስላልተከፋፈለና በየቦታው ቁም የይለፍ ወረቀት አሳይ የሚል ጠባቂ ስላልነበረ አምረው የተሰሩ መንገዶችና የባህር ወደቦች ስለነበሩ ሰባኪዎች ክርስትናን ለማስተማር ወደ ፈለጉበት አገር እንደልባቸው ይሄዱ ነበር፡፡

ሐ) ታላቁ እስክንድር ከሮም መንግስት መስፋፋት ቀደም ብሎ ብዙ ሀገሮችን አንድ አድርጎ በመግዛቱና በርሱም ዘመን የግሪክ ቋንቋ በዓለም ተስፋፍቶ ስለነበር ወንጌልን ለመስበክ ጠቀመ፡፡ ሐዲስ ኪዳንም የተጻፈው በጽርዕ ፣ በሮማይስጠና በዕብራይስጥ ቋንቋ ስለነበር ይህም አንድ ምክንያት ነበር፡፡

መ) ከፍልስጥኤም ውጭ ይኖሩ የነበሩት አይሁድ የፋሲካንና የእሸት በዓል (በዓለ ሰዊት) ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ሳለ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በተሰጠበት ቀን በጴጥሮስ ስብከት ክርስትናን የተቀበሉ ወደ የመጡበት ሀገር ተመልሰው የተማሩትን በማስተማራቸው የክርስትና ትምህርት ሊስፋፋ ችሏል፡፡

ሠ) ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ (1÷22-23) እንደሚገልጸው በዚያን ጊዜ የነበረው ሕዝብ በግብረገብነት በጣም ተበላሽቶ ነበር፡፡ አገልጋዮችና ሴቶች ለሰው ልጅ የሚገባውን መብት ተገፈው በስቃይ ላይ ነበሩ በዚያ ህዝቡ ለኃጢአት በተገዛበት ዘመን ጳውሎስ በገላትያ (3÷28) በሚያስተምረው መሠረት የክርስቶስ ተከታዮች ወንጌልን ስለሰበኩ ደሀው ሕዝቡ በተለይም ሴቶቹ የክርስትን እምነት በስፋት እየተረዱ በመቀበላቸው፡፡

ረ) ክርስቲያኖች ደሀ፣ሐብታም አሽከር፣ ጌታ ሳይሉ እርስ በእርስ በመፈቃቀራቸውና ሐዋርያት በየቦታው ይሠሯቸው የነበሩ ተአምራት የሕዝቡን አእምሮ ስለማረኩት ብዙ ሕዝብ ክርስትናን ተቀብሎ የክርስትና ሃይማኖት ሊጠናከርና ሊስፋፋ ችሏል፡፡

## የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ሕይወት

በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቤተክርስቲያን በ120ው ቤተሰብ ደርጅታ እንደገናም ከመጀመሪያው የቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት በኋላ ማኅበረ ክርስቲያን ወደ 3ሺ ሲደርሱ በኋላም 5ሺው ተጨምረው 8ሺ ደረሱ፡፡ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ውስጥ በተመሠረተችው ቅድስት ቤተክርስቲያን የክርስቲያኖች ወይም የአማኞች ቁጥር እየበዛ ይሄድ ነበር፡፡ ይኸውም በክርስቲያኖች መካከል የነበረው የእርስ በእርስ ፍቅርና መተሳሰብ በዙሪያቸው የሚኖሩ ያላመኑ አሕዛብን ያስቀናቸውና ይስባቸው ነበር፡፡ በመፈቃቀራቸውም የክርስቶስ ደቀመዛሙርት መሆናቸውን አስመስክረዋል፡፡ቅዱሳን

ሐዋርያትም ከክርስቶስ ጋር አብረው የኖሩ እና በጉባኤያትም ጊዜ የወንጌልን ትምህርት በተለይም የክርስቶስን ትንሳኤ በዓይናቸው ያዩ በመሆናቸው እያረጋገጡ ያስተምሯቸው ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ ስለ መሲህ በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ትንቢቶች በኢየሱስ ክርስቶስ መፈፀማቸውን አስፋፍተው ያስረዷቸው ነበር፡፡ እንዲሁም በየጊዜው ሥጋውን ደሙን በአንድነት እየተቀበሉ አንድነታቸውን አጽንተው ይኖሩ ነበር፡፡ ዮሐ 6÷54 በወንድማማችነት የተሳሰሩ መሆናቸውን ለመግለጽ በአንድነት በአንድ ማዕድ ላይ ተቀምጠው ይመገቡ ነበር፡፡ ይኸውም የሐዋርያት የፍቅር ማዕድ "አጋፔ" ይባል ነበር፡፡ በምእመናን ሁሉ ዘንድ መንፈሳዊ ደስታ፣ትሕትና፣ፍቅርና እነዚህን የመሳሰሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸው ጎልተው ይታዩ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል የማስተማር፣ትንቢት የመናገር፣ተአምራት የማድረግ ኃይል የተሰጣቸው ነበሩ፡፡ የሐዋ 11÷28 ከክርስትና እምነት ውጭ የነበረው ሕዝብ በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ የተደረገውን ታላቅ ለውጥ በማየት ወደ ክርስትና እምነት በብዛት ስለመጣ የክርስቲያኖች ቁጥር እየበዛ ሄደ፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩት ክርስቲያኖች ከመካከላቸው ችግርን ለማስወገድ በማሰብ እየተሳሰቡ ገንዘብ በማዋጣት ችግር የደረሰባቸውን ሁሉ በሚገባ ይረዱአቸው ነበር፡፡ ሀብታሞች ያለአንዳች አስገዳጅ በወንድምነት ፍቅር ተስበው በፈቃዳቸው ርስታቸውን እየሸጡ ለድሆች እንዲያካፍሉአቸው ለሐዋርያት ይሰጡ ነበር፡፡

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱሳን ተቀብለው በይሁዳ ምትክ ማትያስን በሲኖዶስ ሹመው (ሐዋ 1÷26) የማስተማር ሥራቸውን የጀመሩት በዚያው በኢየሩሳሌም አካባቢ ሲሆን የአማኞች ቁጥር እየጨመረ ስለሄደ ክርስቶስን በምቀኝነት የገደሉ ሰዎች በክርስትና ትምህርት መስፋፋት በጣም ተበሳጭተው ከእነርሱ ወገን የነበረ በኋላ ግን በክርስቶስ አምኖ የትንሳኤው ምስክር የሆነ ሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስን ገደሉት፡፡ ሐዋ 7÷8፡፡ ከዚህ በኋላ ክርስቲያኖች ወደተለያዩ ሀገሮች በመበታተናቸው ክርስትና በአካባቢው ሀገሮች እንዲስፋፋ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ሐዋርያትም በኢየሩሳሌም ብቻ ሳይሆን በአንጾኪያና በሌሎችም ከተሞች እየተዘዋወሩ የመዳንን መልእክት ለአይሁድም ለአሕዛብም በማስተላለፍ በሌሎችም ከተሞች እየተዘዋወሩ አስተምረዋል፡፡

## የቤተክርስቲያን ታሪክ በዘመነ ሐዋርያት

ዘመነ ሐዋርያት ብለን የምንጠራው ዘመን በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ ለ120ው ቤተሰብ ከወረደ በኋላ ያለውን ነው፡፡ ሐዋርያት በሁሉም አቅጣጫ ወንጌልን በመስበክ ጨለማው ዓለም ብርሃን የሆነበት አልጫው የጣፈጠበት የክርስቶስ አምላክነት ለዓለም የተነገረበት በአጠቃላይ የድኅነት ዓለም ምስጢር በስብከተ ወንጌል ስርጭት ገሃድ የሆነበት፣የወንጌል ዘርና መከር ወቅት ነው፡፡

ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከታጠቁ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሂዱና አስተምሩ በጨለማ የነገርኋችሁን በብርሃን ተናገሩት በጆሮአችሁ በሹክሹክታ የነገርኋችሁን በሰገነት ላይ ስበኩት፡፡"ማቴ 10÷26 ሲል የሰጣቸውን ትእዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ወጡ ፣ መልካሙን የምስራች ዜና አወሩ የሕይወትንም ቃል ለዓለም አሰሙ፡፡ የዓለምን ጨለማ ለማራቅና አልጫ የሆነውን ዓለም ለማጣፈጥ የሚቻልበትን የብርሃንና የጨውነት ተግባር ፈጸሙ፡፡ ቃለ ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ላይ የተዘራውና ይህ የሕይወት ፍሬ የተመሠረተው በእነዚህ ሐዋርያት የወንጌል ግብርና ስለሆነ ዘመነ ሐዋርያት በእርግጥ ዘመነ ዘርና ዘመነ ፍሬ እንደሆነ በግልጽ ይታያል፡፡

የ12ቱ ሐዋርያት የ72ቱ አርድዕት የ36ቱ ቅዱሳን አንስት በአጠቃላይ በዘመኑ የነበሩትን የ120ውን ቤተሰብ ስም ዝርዝር እንመለከታለን

- 12ቱ ሐዋርያት

1) ጴጥሮስ (ስምኦን ወይም ኬፋ)
2) እንድርያስ እኅሁ ለጴጥሮስ
3) ያዕቆብ ወልደዘብዴዎስ
4) ዮሐንስ ወልደዘብዴዎስ
5) ፊሊጶስ
6) በርተለሜዎስ
7) ቶማስ ዘህንደኬ ዲድሞስ
8) ማቴዎስ (ቀራጭ የነበረው)
9) ያዕቆብ ወልደእልፍዮስ
10) ታዲዎስ (ልብድዮስ)
11) ስምዖን ቀነናዊ (ናትናኤል)
12) የአስቆሮቱ ይሁዳ (በማትያስ ተተክቷል)

እነዚህ ከዓሳ አስጋሪነት፣ ከቀራጭነትና ከግብር አስገባሪነት እንዲሁም ከልዩ ልዩ የሥራ መስክ የተመረጡ ናቸው። ለነዚህም ሥልጣን ሰጣቸው ተአምራትም እንዲያደርጉ ኃይል ተሰጣቸው። ማቴ 10÷2 ፣ ማር 6÷7 ፣ ሉቃ 9÷1 ፣ ሐዋ 1÷23

❖ **ሐዋርያት**

ሐዋርያት የሚለው ቃል የሐዋርያ ብዙ ቁጥር ሲሆን ሐዋርያ ማለትም ሖረ ሄደ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ነው ትርጉሙም የተላከ፣ሂያጅ፣ልዑክ ማለት ነው። ወንጌለ መንግስትን ፣ድኅነተ ዓለምን ለመላው ዓለም ሊያውጁ ወይም ሊያበስሩ ተልከዋልና። መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዘመኑ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ 40 ቀንና 40 ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ ከጾመ ከጸለየ በኋላ የማስተማር ሥራውን ሲጀምር አስቀድሞ ያደረገው ነገር ቢኖር ቃሉን ሰምተው ፣ ተአምራትን አይተው ፣ በአለም ዞረው ወንጌልን የሚሰብኩ ደቀመዛሙርት መምረጥ ነበር። እነዚህ ደቀመዛሙርት ሐዋርያት ይባላሉ። ማር 3÷13

ጌታችን ሐዋርያትን ከድሆችም ከሀብታሞችም መርጦአል። እነ ቅዱስ ጴጥሮስን የመሰለ ደሀ ዓሳ አጥማጅ ሲጠራ እነ ቅዱስ ማቴዎስን የመሰለ በቀረጥ ብር የከበሩትንም አልተዋቸውም። ሁሉም በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ናቸውና።ሁሉም ደግሞ ያላቸውን ትተው ተከትለውታል ማቴ 4÷20 ማቴ 9÷9። ከተማሩትም ከማያምኑትም ወገን መርጧል። ዮሐንስንና ያዕቆብን ጌታ የጠራቸው ከአባታቸው ጋር ዓሳ ሲያጠምዱ ነው። ሌላ ትምህርት አልነበራቸውም ነገር ግን አልናቃቸውም። የቀናተኞች አይሁድ ወገን በመሆኑ በዚያን ዘመን ሮማውያንን ለማስወጣት ውስጥ ውስጡን በምድረ ፍልስጥኤም ይካሄድ የነበረው አመጽ ተካፋይ የነበረው ስምኦንን ከዚያ ግርግር አውጥቶ የሰላምና የጸጥታ ወደብ ወደ ሆነው ወደ እርሱ ጠርቶታል።

ቤተእስራኤል ስትመሠረት 12ቱ አበው እየተባሉ በሚጠሩት ከያዕቆብ አብራክ በተከፈሉ አሥራ ሁለቱ ነገድ አባቶች ነበር። አሁንም በክርስቶስ ፈቃድ የእስራኤል ዘነፍስ ማኅበር ቅድስት ቤተክርስቲያን በ12ቱ ሐዋርያት ተመሠረተች።

❖ ሐዋርያት እስከ መጨረሻው በመጽናት ለክርስቶስ ምስክር ለመሆን የበቁባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች

- በዓይናቸው አይተውታልና
- በእጃቸው ዳስሰውታልና
- ትምህርቱን በጆሮአቸው ሰምተውታልና(ዮሐ 1÷2)
- በእርሱ ተልከዋልና (ማቴ 10÷1-4)
- ከትንሳኤው በኋላም አይተውታልና(ዮሐ 21)
- በስሙ ተአምራት ሲፈጽሙ ኖረዋልና (1ቆሮ 12÷12)

ከዚህ በፊት በሌዋውያን ዘር ይወርድ የነበረውን የብሉይ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት በአዲስ በመተካት ለእነርሱ ሰጣቸው። ዮሐ 20÷22 እነርሱም ጌታችን እንዳስተማራቸውና ቃል ኪዳን እንደገባላቸው ለተከታዮቻቸው ይህንን ሥልጣን በአንብሮተ ዕድና በንፍሐት በመሾም አስተላለፉ። ማቴ 28÷20 ፣ ሐዋ 9÷12 በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዋጀችውን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን በስብከታቸው በሰጣቸው ሥልጣን ባደላቸውም ጸጋ ጠብቀው አቆዩአት። የመጀመሪያ ስራቸውንም በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት 3ሺህ ምዕመናንን ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን በማስገባት በይፋ ጀመሩ። ከዚያም ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ተዘዋውረው አስተማሩ። ወንጌልን ሰብከው ቤተክርስቲያንን አነፁ። አምልኮ ጣዖትን አጠፉ። ርኩሳን አጋንንትን አሳደዱ። በመስቀል እርፍ አርሰው ንጹሕ ዘር ወንጌልን ዘርተው በደማቸው አተሙ። ለአስተማሩት ሕዝብ ለእምነቱ ማጽኛ የሚሆኑ መልእክታትን ጻፉ።ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ደነገጉ ከጌታ የተማሩትን ያዩትንና የሰሙትን

ለተከታዮቻቸው በቃልም በኑሮም በመጻሕፍትም አውርሰው በተጋድሎ ዐረፉ፡፡

❖ **የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ታሪክ**

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትውልዳቸው ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ነው ጴጥሮስና ወንድሙ እንድርያስ አባታቸው ከነገደ ሮቤል ሲሆን እናታቸው ደግሞ ከነገደ ስምኦን ናት፡፡ ያዕቆብ ፣ ወንድሙ ዮሐንስ አባታቸው ከነገደ ይሁዳ ሲሆን እናታቸው ደግሞ ከነገደ ሌዊ ናት፡፡ ፊልጶስ ከነገደ ዛብን ፣ በርተሎሚዎስ ከነገደ ንፍታሌም ፣ ቶማስ ከነገደ አሴር ፣ ማቴዎስ ከነገደ ይሳኮር ፣ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ከነገደ ጋድ ስምኦን ቀነናዊ (በኋላ ናትናኤል የተባለው) ከነገደ ብንያም ፣ ታዲዎስ የተባው ልብድዮስ ከነገደ ዮሴፍ ፣ በይሁዳ ምትክ የገባው ማትያስ ከነገደ ዳን ናቸው፡፡

1) ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ (ስምዖን/ኬፋ)

ቅዱስ ጴጥሮስ የተወለደው በገሊላ ባሕር ዳር በምትገኘው በቤተሳይዳ ነው፡፡ የአባቱ ስም ዮና ይባላል፡፡ ጌታን ከመከተሉ በፊት ከአምስት አመት ጀምሮ ያደገው በቅፍርናሆም ከተማ ሲሆን በጎልማሳነቱ ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር በገሊላ ባሕር ዓሳ አጥማጅ ነበር፡፡ ማር 1÷16-18 ለደቀመዝሙርነት ሲመረጥ ዕድሜው 55 ዓመት እንደነበር ይነገራል፡፡ የመጀመሪያው ስሙ ስምዖን ሲሆን ጌታችን ጴጥሮስ ብሎታል፡፡ በላቲን ቋንቋ አለት በአረማይክ ኬፋ በግዕዝ ኰኵሕ ማለት ነው፡፡ ማቴ 16÷17 የመንግስተ ሰማያት ቁልፍ ተሰጥቶታል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በፍልስጥኤም ፣ በልዳ ፣ በኢዮጴ ፣ በቂሳርያ ፣ በሶርያ ፣ በጳንጦን ፣ በገላትያ ፣ በቀጰደቅያ ፣ በቢታንያ ፣ በሮሜና በተለያዩ ሀገሮች እየተዘዋወረ አስተምሮ አሳምኗል፡፡ ሐዋ 2÷41 ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሮም ንጉሠ ነገሥት ኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግስት በክርስቲያኖች ላይ በተነሳው ስደትና መከራ በመስቀል ተሰቅሎ በሰማዕትነት አረፈ፡፡ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የቤተክርስቲያን ጸሐፊ ቅዱስ ጴጥሮስ በቫቲካን ኮረብታ ጳውሎስ ደግሞ በሮም በአስቲያ መንገድ መቀበራቸውን መስክሯል፡፡ ቅድስት ቤተክርስቲያናችንም የእነዚህን ታላቅ የቤተክርስቲያን መሠረቶች የሆኑ ቅዱሳን አባቶች የዕረፍታቸውን መታሰቢያ በዓል በየዓመቱ ሐምሌ 5 ቀን ተከብራለች፡፡

2) ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ

ቅዱስ ዮሐንስ ሀገሩ ገሊላ አውራጃ ሲሆን ከወንድሙ ከቅዱስ ያዕቆብና ከአባቱ ከዘብዴዎስ ጋር ዓሳ ያጠምድ ነበር፡፡ ማር 1÷19-20 ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ እመቤታችንን እንዲያገለግላት አደራ የተሰጠው ለዮሐንስ ነው፡፡ ዮሐ 19÷26 ጌታ ይወደው የነበረው ዮሐንስ በፍልስጥኤምና በሌሎች ቦታዎች ክርስትና እንዲስፋፋ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በመተባበር አስተምሯል፡፡ ሐዋ 4÷1-22 ፣ 8÷14 ከኢየሩሳሌም ወደ ኤፌሶን በመሄድ በታናሿ እስያ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት በማስተማር ሲያገለግል ቆይቶ በድምጥያኖስ ዘመነ መንግስት ወደ ደሴተ ፍጥሞ ተሰዶ በግዞት ሳለ ራዕየ ዮሐንስን ጽፏል፡፡

3) ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ (ወልደ ዘብዴዎስ)

ቅዱስ ያዕቆብ የዮሐንስ ወንድም ሲሆን የመጀመሪያ ሥራው ከአባቱ ጋር ዓሳ ማጥመድ ነበር፡፡ ማር 1÷19 ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ውስጥ በተመሠረተችው ቤተክርስቲያን መሪ ሆኖ በማስተማር ከፍ ያለ አገልግሎትን አበርክቷል፡፡ በስፔን ሀገርም እንደሰበከ በቤተክርስቲያን የታሪክ መዛግብት ይነገራል፡፡ የክርስትናን ትምህርት በስፋት በማስተማሩ በአይሁድ ዘንድ እንደ ወንጀለኛ ይቆጠር ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሄሮድስ አግሪጳ አይሁድን ለማስደሰት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በ44 ዓ.ም አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡ ሐዋ 12÷2 ቅዱስ ያዕቆብ የኖረውም ያረፈውም በኢየሩሳሌም ከተማ ነው፡፡ ከ12ቱ ሐዋርያት መካከል መጀመሪያ ሰማዕትነትን የተቀበለ ሲሆን ይህም በሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ የተጻፈለት ብቸኛ ሐዋርያ ነው፡፡

- ❖ እነዚህ እስካሁን ከላይ ያየናቸው ሶስት ሐዋርያት ማለትም ጴጥሮስ ፣ ዮሐንስና ያዕቆብ አዕማደ ሐዋርያት (የምስጢር ሐዋርያት) ይባላሉ፡፡ ገላ 2÷9

4) ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ

ቅዱስ እንድርያስ የቅዱስ ጴጥሮስ ወንድም ሲሆን ትውልዱም በቤተሳይዳ ነው። በዓሳ ማጥመድ ተግባር ላይ ሳለ በጌታ ቃል በመጀመሪያ የተጠራ ነው። ዮሐ 1÷35-45 ጌታን ከመከተሉ በፊት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዝሙር ነበር ዮሐ 1÷41 ቅዱስ እንድርያስ መጀመሪያ የስብከት ሥራውን በፍልስጥኤም ጀመረ። የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የነበረው አውሳብዮስ እንደገለጠው እንድርያስ በሩስያ ወንጌልን ሰብኳል። ቀጥሎም በቢታንያ ፣ በገላትያ ፣ በሩማንያ ፣ በመቄዶንያ ፣ በታናሽ እስያ ፣ በግሪክ አገሮች አስተምሯል። የቁስጥንጥንያን ቤተክርስቲያን የመሰረተና የቁስጥንጥንያ የመጀመሪያ ሊቀጳጳስ መሆኑ በቤተክርስቲያን ታሪክ ይነገራል በመጨረሻም ግሪክ ውስጥ ምትሩ ለምትባለዋ ሀገር ሲያስተምር በጣዖት አምላኪዎች እጅ "ረ" የሚመስል ቅርጽ ባለው መስቀል ተሰቅሎ በድንጋይ ተወግሮ ታህሳስ 4 ቀን በ80 ዓ.ም በሰማዕትነት አርፏል።

5) ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ

ቅዱስ ፊልጶስ ሀገሩ ቤተሳይዳ ነው። ዮሐ 1÷14 ጌታ ተከተለኝ ባለው ጊዜ ወዲያውኑ ጥሪውን በመቀበል ጌታን ከመከተሉም በተጨማሪ ናትናኤልን ወደጌታ ያቀረበ (የጠራ) እርሱ ነው። የሐ 1÷46-47 ጌታችንን ለማየት የፈለጉት ከአህዛብ ወገን የነበሩት ግሪኮች ለመጀመሪያ ጊዜ ቀርበው የተማሩት በፊልጶስና በእንድርያስ አቅራቢነት ነበር። ዮሐ 12÷2-22 ሐዋርያው ወንጌልን በታናሽ እስያ ውስጥ በምትገኘው በፍርግያ አስተምሯል። በመጨረሻም በታናሽ እስያ ሲያስተምሩ በተቃዋሚዎች እጅ ተሰቅሎ ዐርፏል።

6) ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ /ዲዲሞስ/

ሐዋርያው ቶማስ በፋርስና በሕንድ አስተምሯል። ሕንድ የደረሰው በ46 ዓ.ም ገደማ ነው። ጌታ ከሙታን እንደተነሳ ለሐዋርያት በተገለጠበት ጊዜ ቶማስ ስላልነበረ ከሞት መነሳቱን ሐዋርያት ሲነግሩት ሳላይ አላምንም አላቸው። ጌታ ሁሉም ባለበት እንደገና ተገልጦ ቶማስ በጣቱ የጌታን የተወጋ ጎኑን ፣ የተቸነከረውን እጅና እግሩን ዳስሶ አምኗል። "ጌታዬ አምላኬ" ብሎም መስክሯል ዮሐ 20÷14-29 መምልኪያነ ጣኦት በ86 ዓ.ም የቅዱስ ቶማስን ቆዳውን ገፈው ስልቻ በመስራት በሰውነቱ ላይ ጨው ነስንሰው በአሰቃቂ ሁኔታ እንደገደሉት ታሪክ ይመሰክራል። ስንክሳር ዘወርኀ ግንቦት ገጽ 336-341

7) ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ

ጌታን ከተከተለ በኋላ የወንጌልን ትምህርት በአረብ ፣ በሕንድ ፣ በአርመንያና እንዲሁም በአካባቢዋ አስተምሯል። የአርመን መንበር ያቋቋመው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ነው። በተአምራቱና በትምህርቱ ብዙ ክርስቲያኖችን በማፍራቱ በቅናት ሰዎች ተነስተውበት መስከረም አንድ ቀን አሸዋ በተሞላ ከረጢት ውስጥ ከተው ከነሕይወቱ ባህር ውስጥ ጣሉት። በዚያም ዐረፈ በነገውም ክርስቲያኖች ምእመናን ከባህር አውጥተው እንደቀበሩት የቤተክርስቲያን የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ።

8) ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ(ሌዊ)

ቅዱስ ማቴዎስ የመጀመሪያ ስሙ ሌዊ ነው። ማር 2÷14 ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣለት ጌታ ነው። ማቴዎስ የቀድሞ ሥራው ቀራጭ /ግብር ሰብሳቢ/ ነበር። ማቴ 9÷9 የቀረጥ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ጌታ ጠጋ ብሎ "ተከተለኝ" አለው። ወዲያው በቤቱ ታላቅ ግብዣ ለጌታ አድርጎ ጓደኞቹ የነበሩትን ቀራጮችን ወደጌታ አቅርቦ ካገናኛቸው በኋላ ሁሉንም ትቶ ተከተለው። ሉቃ 5÷27-32 በዚህም አንዳንዶች ማቴዎስን የቁም ተዝካሩን አውጥቶ ጌታን የተከተለ ሐዋርያ ይሉታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ለስብከት ሲሰማራ በዕጣ የደረሰችው ሀገር ምድረ ፍልስጥኤም ስትሆን ቀጥሎ በኢትዮጵያ ፣ በፋርስ ፣ በባቢሎን አካባቢ እንደሰበከ ይነገራል። /ገድለ ሐዋርያት ገጽ 101/ ቅዱስ ማቴዎስ የአይሁድና የአረማውያንን ትምህርት እየተቋቋመ ድውያን ሲፈውስ ፣ አጋንንትን ሲያወጣ ልዩ ልዩ ተአምራትን ሲያደርግ ዝናው በከተማ ሁሉ በመዳረሱ በዚህ የተናደዱ መኳንንት የሞት ፍርድ ፈረዱበት ጥቅምት 12 ቀን አንገቱን በሰይፍ ተሰይፎ ዐረፈ።

9) ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ /ወልደ እልፍዮስ/

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ጸሎት ወዳድ ስለነበር ለብዙ ሰዓታት መቆም ስለሚያበዛ እግሩ ያብጥበት ነበር። ከዚህ የተነሳ እንደሌሎች ሐዋርያት ተዘዋውሮ ማስተማር ባለመቻሉ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ በመሆን ተሾመ። /ገድለ ሐዋርያት ገጽ 73/ በ50 ዓ.ም አካባቢ በኢየሩሳሌም የተደረገውን ሲኖዶስ በሊቀ መንበርነት የመራው እርሱ ነው።

ሊቀካህናቱ አይሁድን ሰብስቦ ያዕቆብ ክርስቶስን ክዶ እንዲያስተምር ቢጠይቀው ቅዱስ ያዕቆብ ጌታን በመካድ ፈንታ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ስራ ጌትነቱንና አምላክነቱን መስክሯል። በዚህ የተናደዱት የአይሁድ አለቆች ያዕቆብ ከቤተመቅደስ ጫፍ ወደ ምድር ወረወሩት። ከዚያም ከሥር ያሉ አይሁድ በድንጋይ ወግረው የካቲት 10 ቀን 82 ዓ.ም ገደሉት።

**10)** ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ/ልብድዮስ/

የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ በመባል ይታወቃል፡፡ ሐዋ 1÷13 ፣ ሉቃ 6÷16 ታዴዎስ ልብድዮስ እየተባለም ይጠራል፡፡ ማቴ 10÷4 የሐዋርያው ታዴዎስ ሀገረ ስብከት ሶርያ ሲሆን በተጨማሪም በፍልስጥኤም ፣ በአርመንና በፋርስም አስተምሯል፡፡ ወደ ሀገረ ስብከቱ ሶርያ ሲጓዝም ቅዱስ ጴጥሮስ አብሮት ነበር፡፡

ሐዋርያው ታዴዎስ ተአምራትን ሲያደርግና ሲያስተምር ቆይቶ ሐምሌ 2 ቀን በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡ /ስንክሳር ሐምሌ 2/

**11)** ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ

ሐዋርያው ማትያስ ጌታን በሸጠው በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ የተሾመ ሐዋርያ ነው፡፡ ሐዋ 1÷15-26 በቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊነት የታወቀው አውሳብዮስ ቅዱስ ማትያስ ከሰባው አርድዕት ወገን እንደነበር ጽፏል፡፡ /አውሳብዮስ 1÷13/

ማትያስ ለሐዋርያነት እንዲመረጥና ዮስጦስ ሶርስያ ከተባለው ከዮሴፍ ጋር ዕጣ እንዲጣጣል ሐሳብ ያቀረበው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደተናገረው ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስካረገበት ቀን ድረስ ከሐዋርያት መካከልም በገባበትና በወጣበትም ዘመን ሁሉ ማትያስ ከሐዋርያት ጋር ነበር፡፡ ሐዋ 1÷21-22

ቅዱስ ማትያስ ወደ ደማስቆ ሄዶ ወንጌልን ሲያስተምር በአይሁድና በአረማውያን ቅስቀሳ ተቃዋሚዎች ተነስተው በብረት አልጋ ላይ በማስተኛት ከታች ለሰባት ቀናት ያህል እሳት አነደዱበት፡፡ በሰባተኛው ቀን ሂደው ቢመለከቱት ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስበት አገኙት፡፡ በዚህን ጊዜ ይህንን ስቃይ ይፈጽሙበት የነበሩ ሰዎች በክርስቶስ አምነው ተጠምቀዋል፡፡ የቅዱስ ማትያስንም እውነተኛ ሐዋርያነት ተረድተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ማትያስ በሀገረ ይሁዳ ሲያስተምር ከኖረ በኋላ ፈላዎን በተባለች ቦታ በሽምግልና ዘመኑ አርፎአል፡፡ ሐዋርያው ማትያስ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጋቢት 8 በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደግሞ ነሐሴ 9 ቀን (እ.ኤ.አ) ይከበራል፡፡

**12)** ሐዋርያው ናትናኤል

የተወለደው ናዝሬት በምተገኘው በቃና ዘገሊላ ነው፡፡ዮሐ 1፡2 የመጀመሪያው ስሙ ስምዖን ሲሆን ናትናኤል ብሎ የጠራው ጌታ ነው፡፡የትውልድ ዘመኑ ጌታችን በተወለደበት ዘመን አካባቢ እንደሆነ ይነገራል ምክንያቱም ሄሮድስ የቤተልሔም ህጻናትን በሚያስፈጅበት ጊዜ እናቱ ከበለስ ስር ደብቃ አትርፋዋለች ጌታም “ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ስር ሳለህ አውቅሃለሁ” ያለው ለዚህ ነው፡፡ወደ ጌታ የጠራው ፊልጶስ ሲሆን ናትናኤል የኦሪት ምሁር ነው፡፡ መጻሕፍትንም በማወቁ “ከናዝሬት መልካም ነገር ይወጣልን?”በማለት የነቢያትን ቃል ተናገረ፡፡ዮሐ 1፡44-52

ሐዋርያው ናትናኤል/ስምዖን/ ወንጌልን በሶሪያ በባቢሎን በግብጽና ሊቢያ እየተዘዋወረ አስተምሯል፡፡ማቴ 10፡4 በመጨረሻም በግብጽ ሲያስተምር ሕዝቡ በትምህርቱ አምነው በመብዛታቸው አረማውያኑ ስለቀኑበት ለግብጹ ንጉሥ እንድርያኖስ ከሰሰው በሠራዊት በማስያዝ በንጉሡ ትእዛዝ ሐምሌ 10 ቀን በሰይፍ አስገደሉት፡፡/ስንክሳር ሐምሌ 10/

- ቅዱስ ጳውሎስ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተወለደው ጠርሴስ ከተማ ሲሆን ትውልዱ ከዕብራውያን ከብንያም ነገድ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በ15 ዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ ከገማልያል የአይሁድን ሕግና ሥርዓት ጠንቅቆ ተምሯል፡፡ በአይሁድ ሸንጎ አባልነት ለሁለት ዓመታት በሠራበት ወቅት ለኦሪት እምነቱ ቀናተኛ ፈሪሳዊ በመሆኑ ክርስቲያኖችን በማናቸውም አጋጣሚ ይቃወም ነበር፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በደማስቆ ያሉ ክርስቲያኖችን ለማሳደድ የፈቃድ ደብዳቤ ከሊቀ ካህናቱ ተቀብሎ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት በመንገድ ሲሄድ ከከተማ ሳይገባ ድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን መጥቶ አካባቢውን አበራው፡፡ ጳውሎስም ወደ መሬት ወደቀ፡፡ "ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ ፣ የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም ጌታ ሆይ አንተ ማነህ? ብሎ በጠየቀ ጊዜ የምታሳድደኝ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ፡፡ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል" ብሎ ጌታችን

ተናገረው ጳውሎስም የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ከነገረው በኋላ ደማስቆ እንዲገባ አስታወቀው። ሐዋ 9÷11 ሐናንያም ወደርሱ ተልኮ በወደቀ ጊዜ የተጋረደበትን ካይኑ እንደቅርፊት እንዲወድቅ ካረገ በኋላ አጥምቆና አስተምሮ ለአገልግሎት ዝግጁ አደረገው። ቅዱስ ጳውሎስም አረብ ሀገር ሄዶ ሶስት ዓመት ከቆየ በኋላ ወደ ደማስቆ ተመልሶ መስበክ ጀመረ። አይሁድ በቅናት ተነሳስተው ሊገሉት ሲያሳድዱት የደማስቆ ክርስቲያኖች ከከተማዋ ቅጽር በቅርጫት አውርደው ወደ ኢየሩሳሌም ላኩት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ካደረጋቸው ጉዞዎች

- የመጀመሪያው ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ከተመለሰ በኋላ በልዑል እግዚአብሔር ጥሪ በአሕዛብ ሀገር ወንጌልን ለመስበክ ከበርናባስ ጋር ወጡ። ሐዋ 13÷1-3 በዚህ ጉዞአቸው በጠቅላላ ወደ 2 ሺህ ኪ.ሜ የሚደርስ መንገድ በእግር ተጉዘዋል። ጉዞው የተከናወነው በ46 ዓ.ም አካባቢ ሲሆን ከ14 የማያንሱ ሀገሮች ተጎብኝተዋል።

- ሁለተኛው ጉዞ በ50 ዓ.ም ገደማ ከሲላስ ጋር ያደረገው ጉዞ ነው። በጉዞው ከ18 የማያንሱ ከተሞች የተጎበኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ገላትያ ፣ ጢሮስና ፣ ኤፌሶን፣ ቆሮንቶስ ልስጥራ ፣ ኢየሩሳሌም አንጾኪያ ይገኙበታል። ደቀመዝሙሩን ጢሞቴዎስን ያገኘው በዚህ ጉዞው በልስጥራ ከተማ ሊያስተምሩ ነው።

- ሶስተኛውን ጉዞ ያደረገው በ54 ዓ.ም ሲሆን ብዙ ሀገሮችን በጉዞው አካትቷል። በዚህ ጉዞው ከልዩ ልዩ ሀገር ክርስቲያኖች የሰበሰበውን ዕርዳታ ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ይዞ ሲመለስ በኢየሩሳሌም የፋሲካ በዓል ስለነበር ከየሀገሩ የመጡ አይሁድ ቅዱስ ጳውሎስን ተቃወሙት ተቃውሞውን ለመግታት በአይሁድ ህግ በቤተመቅደስ የመንጻት ስርዓት መፈጸም ጀመሩ። ነገር ግን ከአህዛብ ወገን የነበረውን ደቀመዝሙሩን ጢሞቴዎስን ወደ መቅደስ ያስገባው መስሏቸው ተቃውሟቸው በረታ። በዚህ የተነሳ ከተማዋ ታወከች። ሐዋ 2÷29 በሁከቱ የተነሳ ሐዋርያው ጳውሎስ በ58 ዓ.ም ለሮም እስር ተዳርጓል። ሁለት ዓመት በቁም እስር ቆይቶ ከሮማ ህግ ጋር የሚቃወም ምንም ዓይነት ወንጀል ስላልተገኘበት በነጻ ተለቅቋል።

  ከዚህ በኋላ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ ያልተመዘገበውን ጉዞውንም ያደረገው በመታሰሩ ያዘኑትን ክርስቲያኖች ለማጽናናትና የጀመራቸውን ሥራዎች ፍጻሜ ለማየት ነው። በመጨረሻም በኔሮን ቄሳር ዘመን የሮም ከተማ ስትቃጠል ይህንን ያደረጉት ክርስቲያኖች ናቸው በማለት በክርስቲያኖች ላይ የሞት አዋጅ ታውጆ ስለነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኒቆጳልዮን ከተማ ሲያስተምር በ፷፭ ዓ.ም ተይዞ 2 ዓመት ከ6 ወር በጨለማ ቤት በእስር ከቆየ በኋላ በሮም ከተማ ከኦስትያ መንገድ አንገቱን ተሰይፎ በ፷7 ዓ.ም ሐምሌ 5 ቀን በሰማዕትነት አርፏል።

**የሐዋርያት መንበርና ሀገረ ስብከት**

ሀ) የኢየሩሳሌም መንበር

ክርስትና መጀመሪያ የተሰበከው በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ስለነበር የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከተማዋን በማዕከልነት ይጠቀሙባት ነበር። የኢየሩሳሌሙ መንበር የመጀመሪያ ፓትርያርክ ቅዱስ ያዕቆብ (የጌታችን ወንድም የተባለው) ሲሆን በ62 ዓ.ም በሰማዕትነት ሲያርፍ ወንድሙ ስምዖን በመንበሩ ተተካ እርሱም በ106 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ከተማ በሰማዕትነት አርፎአል። ጌታችን በትንቢት እንደተናገረው /ማቴ 23÷37-38/ በ70 ዓ.ም ሮማዊ ንጉስ ጥጦስ ፹ ሺ ሠራዊት አዝምቶ ከተማዋን በመውረር ከተማዋን ሰብሮ ገብቶ በዚያን ጊዜ በሮማውያን አገዛዝ ላይ አምፀው የነበሩትን አይሁድ ግማሾቹን ሲፈጃቸው የቀሩትን ደግሞ በባርነት ሸጣቸው። ከተማዋንም አፈረሳት። በዚህም የተነሳ የኢየሩሳሌም መንበር በመጠኑም ቢሆን ቀዝቅዞ ነበር።

ለ) የአንጾኪያ መንበር

አንጾኪያ ለሮም አስተዳደር ሶስተኛ ከተማ የነበረች የሶርያ ከተማ ነች። በዚህች ቦታ ቀድመው ወንጌልን የሰበኩት ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ በርናባስ ሲሆኑ ቅዱስ ጴጥሮስም ሰብኮባታል። በከተማዋ አይሁድም አህዛብም ነበሩባት። የጌታ ደቀመዛሙርት ክርስቲያን የሚለውን ስም ያገኙት በዚህች ከተማ ነው። ሐዋ 11÷2 ለመጀመሪያዋ የሐዋርያት ሲኖዶስ

ምክንያት የሆነው ጥያቄ የተነሳው ለአንጾኪያ ክርስቲያኖች ነው። በሐዋርያት እግር ተተክቶ መንበሩን የተረከበው አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ነበር። ዛሬ የሶርያ ክርስቲያኖች መንበር ናት።

ሐ) የእስክንድርያ መንበር

የእስክንድርያ ከተማ በግብጽ ሰሜናዊ ጫፍ በአባይ ወንዝ ዳርቻ የምትገኝ ወደብ ናት። ከተማዋ ስሟን ያገኘችው ከታላቁ የመቄዶንያ ተወላጅና የግሪኮች ንጉስ ከነበረው ከእስክንድር ነው። መንበሩን የመሰረተው ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ በ፷ ዓ.ም ነው በ፷፰ ዓ.ም በሰማዕትነት ሲያርፍ ቅዱስ አንያኖስ በመንበሩ ተተክቶአል። ዛሬ የግብጽ ቤተክርስቲያን ዋና ማዕከል ናት።

መ) የሮማ መንበር

የሮም መንግስት ዋና ከተማ ናት። በዚህችም ከተማ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን በስፋት እንደሰበከና የመጀመሪያዎቹ ጳጳሳት ቅዱስ ሌናስንና ቅዱስ አኔቅሊጠስን እንደሾማቸው ይነግረናል። የሮም ሰዎች በሮም ከተማ በመጀመሪያ የሰበከው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሆነ ይናገራሉ።

ሠ) የኤፌሶን መንበር

በጥንቱ የታናሹ እስያ በዛሬው የቱርክ ግዛት የምትገኝ ከተማ ናት። አስቀድሞ በዚህች ከተማ ወንጌልን የሰበከው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊም መንበሩን ኤፌሶን አድርጎ ለብዙ ዓመታት አስተምሮባታል። በመጨረሻም በሮማውያን ተይዞ ወደ ፍጥሞ ደሴት የተጋዘው በዚህች ከተማ ሲያስተምር ነው። የኤፌሶን መንበረ ቅዱስ ዮሐንስ ከዚህ ዓለም ከተለየ ከ፺፱ ዓ.ም በኋላ ቀዝቅዛለች።

ረ) የሰርምኔስ መንበር

በቅድሚያ በዚህች ከተማ በማስተማር መንበሩን የመሰረተው ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ሲሆን እርሱ እየተዘዋወረ ለማስተማር እንዲያመቸው ደቀመዝሙሩ ፓሊካርፐስን በሰማዕትነት እስካረፈበት እስከ 155 ዓ.ም ድረስ ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾሞት ያገለግል ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ማዕከልነቱ እየቀዘቀዘ መጣ። ዛሬ ከተማዋ ኢዝማር ተብላ ቱርክ ውስጥ ትገኛለች።

ሰ) የአቴና መንበር

በመጀመሪያ ለአቴናውያን ወንጌልን የሰበከው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው። እርሱም ለአቴና መንበር ቅዱስ ዲዮናስዮስን ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾመው። በመጀመሪያው መ/ክ/ዘ የአቴና መንበር ወደ ሮም መጠቃለል በመጀመሩ እየቀዘቀዘ መጥቶ ነበር።

ሽ) የቁስጥንጥንያ መንበር

የቁስጥንጥንያ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ የተሰበከችው በሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ነው። ከተማዋ የምሥራቃዊ ሮም ግዛት (የቢዛንታይን) መናገሻ ነበረች። ይህች መንበር እና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን የመሰሉ ታላላቅ የተዋህዶ ሊቃውንት ያፈራች ናት። በ1445 ዓ.ም በኦቶማን ቱርክ ወረራ አካባቢው ሲያዝ የቁስጥንጥንያ መንበርነት ተደመደመ። የቅድስት ሶፍያ ቤተክርስቲያንም መስጊድ ሆነ ስሟም ተቀይሮ ኢስታንቡል በመባል ትታወቃለች።

## ምዕራፍ ሦስት

## ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ሰማዕታት

ቤተክርስቲያን ተጋድሎ በዘመነ ሐዋርያት በአብዛኛው በአይሁድ የመጣ ፈተና ነበር። አይሁድ ክርስትና እንዳይስፋፋ ለማድረግ ሐዋርያትን ማሳደድ ቢጀምሩም ማህበረ እስጢፋኖስን ቢበትኑም ክርስትና እንዳይስፋፋ ለማድረግ ከቶውንም አልቻሉም። ይልቁንም አይሁድ መጽሀፍትና ሕግ ያላቸው የነቢያትም ትንቢት የሚያውቁ ስለሆነ ከእነርሱ ጋይ የሚደረገው ውይይት ክርክር ቀለል ያለ ነበር። ሐዋርያትም የመጽሐፍ ክፍል እየጠቀሱ ለማብራራት አልተቸገሩም ነበር። ክርስትናን

በአህዛብ ምድር ሲሰበክ ግን በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ መከራ ደርሶባታል። አህዛብ ሕግ ያልነበራቸውና የሚመራቸው መጽሐፍ ስላልነበራቸው የደረሰባቸው ፈተና ከበፊቱ እጅግ የበዛና ከባድም ነበር። ቤተክርስቲያን ከአህዛብ ጋር ያደረገችውን ትግልና በአላውያን ነገስታት አማካኝነት የደረሰባትን መከራና ክርስቲያኖች የተቀበሉትን የሰማዕትነት አክሊል በዚህ ምእራፍ እንመለከታለን።

- **ቤተ ክርስቲያንና ነገስታተ አህዛብ**

የክርስትና ሃይማኖት በአህዛብ ምድር መሰበክ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ለውጦች እየመጡ በመላው ሮምም የክርስትና ሃይማኖት ተስፋፍቶ ነበር። በመሆኑም፦

- ለባሮች የነጻነት ትምህርት ተሰበከላቸው
- ባለጸጎች ቢያምኑ የክርስቶስ ባሮች ለመሆን እንደሚበቁ ተነገራቸው
- በአህዛብ ልማድ በወንዶች መካከል ሴቶች የክብር ቦታ ያልነበራቸው ሲሆን በክርስትና ግን እኩልነትና መከባበር ታውጆላቸውል።

ቤተ ክርስቲያን በአስተምህሮዋ ይህን ሁሉ ነገር ብታስተካክልም ጉዞዋን ለማሰናከል በአህዛብ ነገስታት ፈተናና መከራ ደርሶባታል። በክርስቲያኖች ላይም የመብት ጥሰት ቀርቦባቸዋል።

- ✓ ክርስቲያኖች ጣዖትን ማምለክ ትተው እግዚአብሔርን በማምለካቸው ከሀዲዎች ተባሉ።
- ✓ ሰዎች በግፍ ወደ ተራቡ አናብስት ወደሚጣሉባቸው ሰዎችና አውሬዎች ወደሚዋጉባቸው ቲያትር ቦታዎች ባለመሄዳቸው ግማሽ ሰው ተባሉ።
- ✓ የጌታን ስጋና ደም በመቀበላቸው ሕጻናትን እያረዱ ደማቸውን ይጠጣሉ። ስጋቸውን ይበላሉ ተባሉ።
- ✓ በሮም ግዛት ውስጥ ረሀብ፣ ቸነፈር የመሳሰሉት ነገሮች በደረሱ ጊዜ በክርስቲያኖች ምክንያት የሮም አማልክት ተቆጥተው ነው እያሉ ይወነጅሏቸው ነበር።

በዚህ የተነሳ በክርስቲያኖች ላይ በብዙ አላውያን ነገስታት ብዙ መከራና ስቃይ እንዲሁም ሞት ደርሷል። የመጀመሪያውና ብዙ ክርስቲያኖችን ያስፈጀው ንጉስ ኔሮን ቄሳር ነው ከእርሱም ቀጥለው የተነሱና የክርስትናን ሃይማኖት የተቃወሙ የነበሩ ንጉሶችን በየዘመናቸው እንመለከታለን።

- **ቤተ ክርስቲያን በኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግስት /ከ57-68ዓ.ም/**

ኔሮን አሮጌውን ከተማ አዲስ ከተማና ሰፊ ቤተመንግስት እንዲሰራ በማሰብ በ5 ዓ/ም የሮምን ከተማ 2/3ኛውን በእሳት አቃጥሏል። በዚህም የተነሳ በሀብቱ መቃጠልና በዘመዶቹ መሞት ከተቆጣው ህዝብ ለማምለጥ በሀሰት ይህን ቃጠሎ ያስነሱት ክርስቲያኖች ናቸው በማለት ክርስቲያኖች ላይ አመካኝቶባቸዋል። ክርስቲያኖች ላይም ብዙ ስቃይና ሞት አድርሶባቸዋል። በዚህ ዘመን ቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስም ብዙ ተጋድሎ ፈጽመው በሰማእትነት አርፈዋል።

❖ **ቤተክርስቲያን በድምጥኖስ ዘመነ መንግስት /81-96ዓ.ም/**

ድምጥኖስ ከኔሮን ቀጥሎ በክርስቲያኖች ላይ ብዙ መከራና ስቃይ በማድረስ የታወቀ ነው ድምጥያኖስ የራሱን ምስል አሰርቶ እንዲሰግዱለት ወደ ኤፌሶን ልኮት ነበር ያን ጊዜ በኤፌሶን የነበረው ወንጌላዊው ዮሐንስ እና በኤፌሶን የነበሩ ክርስቲያኖች ተቃውመውት ነበር በዚህም የተነሳ ዮሐንስ ለእስራትና ለእንግልት ክርስቲያኖችንም ለመከራ እንዲዳረጉ አድርጓቸዋል፡፡

❖ **ቤተ ክርስቲያን በትራጀን ዘመነ መንግስት /98-117ዓ.ም/**

በትራጀን ዘመነ መንግስት ክርስቲያኖችን በሀይል ብቻ ሳይሆን በዘዴና በማስፈራራትም ጭምር ወደ ቤተ ጣኦት ለመመለስ ይሞክር ነበር በዚህ ዘመን ቅዱስ አግናጥዮስ ሰማእትነቱን ተጋድሎ ፈጽሟል በቲያትር ማሳያ ቦታ ለነበሩ አናብስት ተጥሏል ለዚህም ነው ምጥው ለአንበሳ የሚል ስም ያገኘው፡፡

❖ **ቤተ ክርስቲያን በማርቆስ ኦሬሊስ (አውሬሊያስ) ዘመን /101-180ዓ.ም/**

ማርቆስ ኦሬሊስ ፈላስፋ ነበረ ንጉስ ሲሆን ክርስቲያኖችን በጣም ይንቅና ያንቋሽሽ ነበረ እንዲሁም ከ180-192 ዓ.ም ድረስ የነገሰው ቄሳር ከሞዶስ ባይሳካለትም በስጋዊ ጥበብና ዘዴ ለመተቀም ቤተ ክርስቲያንን ለማትፋት እቅድ ነበረው ነበር፡፡ ሌሎችም እስክንድርሳዊ ሮስ ከ202-205 እነ ፊሊጶስ ዓረባዊ ከ244-249 ዓ.ም ያሉት ነገሥታት ክርስቲያኖችን ንቀውና ተጸይፈው ያሳድዳቸው ይገሏቸው ነበር፡፡

❖ **ቤተ ክርስቲያን በዳክዮስ ዘመነ መንግስት /249-251 ዓ.ም/**

በየዘመኑ ከነበሩ ቄሳሮች ከበድ ያለ አዋጅ በማሳወጅ ክርስቲያኖች መከራ የገጠማቸው በዳክዮስ ዘመን ነበር፡፡ ዳክዮስ የክርስቲኖችን መመሪያ አጥንቶ ከአማካሪዎቹ ጋር ተመካክሮ የሚከተለውን አዋጅ አውጇል፡፡ አዋጁም **‹‹በሮም ግዛት በሮማዊ ዜግነት የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በሮም ባህል መሰረት የሮማ መንግስት ሕጋዊ ነው ብሎ የተቀበለውንና ነገስታቱም ሲያመልኳቸው የነበሩ ጣኦታትን በግዴታ እንዲያመልኩና መባዕ እንዲያቀርቡ የሚል ነበር፡፡ይህን ያልፈጸመ ሁሉ በሞት እንዲቀጣ የሚል** ነበር›› ክርስቲያኖቹም ለዚህ አዋጅ ተገዢ ስላልነበሩ ህይወታቸው በሰማዕትነት እንዲያልፍ ሆኗል፡፡ ከዚህ ዘመን ጀምሮም ክርስቲያኖች ከስቃይ ለማምለጥና ሃይማኖታዊ ተልእኳቸውን ለመፈጸም እንዲችሉ በተለይም በሮምና በአካባቢዋ ዐለት በመፈለግ በአካባቢው ዋሻ በማዘጋጀት ወደ ግበበ ምድር የገቡት፡፡

❖ **ቤተ ክርስቲያን በደዮቅልጢያኖስ ዘመነ መንግስት /284-305ዓ.ም/**

ከላይ ከተገለጹት ቄሳሮች በኋላ በአይነቱም ሆነ በግፉ ተወዳዳሪ የሌለው የክርስቲያኖች እልቂት የተፈጸመው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ነበር፡፡ ዲቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን አጥብቆ እንዲጠላ ያደረጉት ሁለት ነገሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

ጋሌርዮስ የተባለ የልጁ ባል (አማቹ) ክርስቲያኖች አጥብቆ ስለሚጠላ በእርሱ ምክር በመመረዝ እና እንደ ሌሎቹ ቄሳሮች የራሱን ምስል አሠርቶ ስገዱልኝ በማለቱ ክርስቲያኖች ደግሞ አንሰግድም በማለታቸው ነው፡፡

በዚህም ተነሳ ክርስቲያኖችን ከጦር ሰራዊቱ አባሯቸዋል እንዲሁም ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት እነዚህን አዋጅ አሳውጇል፡፡

- አብያተ ክርስቲያናት እንዲደመሰሱ
- ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው እንዳይገናኙ
- ስለክርስትና ሃይማኖት የሚናገሩ መጽሐፍት በጠቅላላ እንዲቃጠሉ
- የቤተክርስቲያን ንብረት የሆነ ሁሉ እንዲወረስ
- ማንኛውም የሮማ ዜጋ ክርስቲያን ከሆነ ከመንግስት ሥራው እንዲወገድ
- ባሮች ክርስትናን ከተቀበሉ ነፃ የመውጣት መብት እንዳይኖራቸው
- ክርስቲያኖች ምንም ህጋዊ ምክንያት ቢኖራቸው በማንም ላይ ክስ መመስረትና ስለ መብታቸው መከራከር አይችሉም የሚል ነበር፡፡

የወጡትን አዋጆች አናከብርም ባሉ ክርስቲያኖች ላይ ደማቸውን አፍስሷል ለአራዊትም ሰጥቷቸዋል ሞትም ፈርዶባቸዋል፡፡ይህን ሁሉ መከራና ስቃይ ካደረሰ በኋላ የዲዮቅልጢያኖስ ዙፋን እያዘመመና እየወረደ ሲሄድ በ305 ዓ.ም

ስልጣኑን ለአማቹ ለጋሌርዮስ ለቆ ወደ ግል የሥጋዊ ኑሮ ተመለሰ። ቤተክርስቲያን ከብዙ የመከራና የስደት ዓመት በኋላ በመጠኑም እረፍት ያገኘችው በታላቁ በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግስት ነው።

❖ **ቤተክርስቲያን በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግስት**

ቆስጠንጢኖስ አባቱ ኮንስታንቲዮስ (ቁንስጣ) እናቱ እሌኒ ትባላለች። በ258 ዓ.ም የተወለደ ሲሆን እናቱ ቅድስት እሌኒ የጌታችንን መስቀል አስቆፍራ ያገኘችው ነች። ቆስጠንጢኖስ በአንድ ወቅት ከጠላቱ ከማክሴንዲየስ ጋር ሊዋጋ ሲሄድ በጉዞ እንዳለ "በዚህ ምልክት ጠላትህን ድል ታደርጋለህ የሚል በመስቀል ቅርጽ ተጽፎ በሰማይ ላይ አየ። በሁሉም የጦር መሳሪያዎቹ፣ በፈረሶቹ ላይ የመስቀል ምልክት አደረገ በዚህም እየተመራ ሄዶ ጠላቱን ድል አደረገ።

ምንም እንኳን አባቱ አህዛብ ቢሆንም እናቱ ግን ክርስቲያን ስለሆነች ክርስትናንም በደንብ ስላስተማረችው እንዲሁም በመስቀል ምልክት ድል ማድረጉን ተከትሎ የበለጠ ስለ ክርስትና እምነት እንዲመረመርና ክርስቲያኖችንም እዲያውቅ አድርጎታል። ከዚያ በኋላ የቆስጠንጢኖስ ሠራዊት የሚለየው በመስቀል ቅርጽ ነው። ለ40 ዓመታት ለ4 ተከፍላ ትመራ የነበረችው የሮም ግዛት በአንድ በቆስጠንጢኖስ ትመራ ጀመር። ቆስጠንጢኖስ የመንግስቱን ስልጣን አንድ አድርጎ መግዛት ከጀመረ በኃላ በክርስቲያኖች ላይ ይደርስ የነበረውን ግፍ አስቁሟል። ለቤተክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርቷን የማስፋፋት ነፃነትን ሰጥቷል። ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስቲያን ከሰጣቸው መብቶች መካከል

- ቤተክርስቲያን ከግብር ነፃ እንድትሆን
- ከመንግስት ገቢ ለቤተክርስቲያን የተወሰነ ድርሻ እንዲኖራት
- እለተ እሑድ (ሰንበት) በንጉሠ ነገስቱ ግዛት ውስጥ ሥራ እንዳይሠራባት አውጇል
- ማንኛውም ክርስቲያን ንብረቱን ለቤተክርስቲያን ማውረስ ይችላል፤ ቤተክርስቲያንም ኑዛዜ የመቀበል ውርስ የመውረስ መብት እንዲኖራት አድርጓል።
- በክርስቲያኖች መካከል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች ችግሮችን ለመፍታት ለኤጲስ ቆጶሳት የዳኝነትን ስልጣን ሰጥቷል።

ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስቲያን ብዙ ውለታ ውሏል። ቅድስት ቤተክርስቲያንም ስለ ብዙ ውለታው ስታስበውና ስትዘክረው ትኖራለች። ቆስጠንጢኖስ ማረፊያው በደረሰ ጊዜ ተጠምቆ ክርስትናን ተቀብሏል ያጠመቀውም ቅዱስ አውሳብዮስ ነው። ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስቲያን ከሠራቸው ዋና ዋና ሥራዎቹ መካከል የሚላኖ ውልና በአርዮስ ምክንያት በተነሳ ብጥብጥ ጉባኤ ማዘጋጀት በጉባኤው ለተገኙ አባቶችም ያሳየው ክርስቲያናዊ ጠባይና ትህትና ተጠቃሽ ናቸው። ቆስጠንጢኖስ በ337 ዓ.ም በግንቦት 22 ዕለት አርፏል።

## ምዕራፍ 4
## ዘመነ መናፍቃን

መናፍቅ ማለት ተጠራጣሪ ማለት ነው። ይህም ማለት በአንድ ሃይማኖት ውስጥ የተለየ ሃሳብ የሚከተል የሆነውን ለማመን የሚያመነታና የሚጠራጠር ወገን መናፍቅ ይባላል። ኑፋቄንም ጥርጣሬን ያመጣው ሳጥናኤል ወይም ዲያቢሎስ ነው ይኸውም የመላእክቱን ነግድ እኔ ፈጠርኩዋችሁ ባለ ጊዜ የተጠራጠሩና የካዱ አሉ እነርሱ መናፍስት ዛሬም ድረስ ሰዎችን ሲያጠራጥሩና ሲያስክዱ ይኖራሉ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ከሮማውያን ነገስታት ከደረሰባት ሥቃይና እንግልት ከውስጧ አማኝ መስለው የውስጥ ጠላቶች ተነስተውባታል ከፍተኛም ጉዳት አድርሰውባታል እነዚህ የቤተክርስቲያን የውስጥ ጠላቶች በጌታ አነጋገር ጸራዊ በሐዋርያት አነጋገር ቢጽ ሐሳዊን በሊቃውንት አነጋገር ደግሞ መናፍቃን ተብለው ይጠራሉ እነዚህ መናፍቃን የቤተ ክርስቲያን ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያን መስለው ወይም የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ግማሹን ይዘው ግማሹን ያልያዙ ጎዶሎዎች ናቸው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ጠላቶች ናቸው ለብዙዎች መናፍቃን መነሻ የሆናቸው ደግሞ የጥንት ግሪኮች የፍልስፍና አስተምህሮ በመሆኑ ይህንኑ አስቀድመን እንመለከታለን

**የጥንት ግሪኮች የፍልስፍና አስተምህሮ**

በዘመኑ ግሪኮች የፍልስፍና ትምህርት እና አስተሳሰብ በአብዛኛው የምዕራቡ ዓለም እንደ እምነት ይታይ ነበር በየዘመኑም የተነሱ ፈላስፎች ስለ ስነ ፍጥረት ስለ ዓለም አኗኗር እና ሁሉን ስላስገኘ ኃይል የተለያዩ መላ ምቶችን በማቅረብ ለተከታዮቻቸው አስተላልፈዋል ይህንንም አስተምህሮዋቸው ለማስፋፋት ይረዳቸው ዘንድ በተለያዩ ቦታዎች ትምህርት ቤቶችን ከፍተው ነበር በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብቶ ያልተማረ ሰው በግሪኮች ዘንድ እንደ ሙሉ ሰው አይቆጠርም ነበር

ከአስተምህሮአቸው መካከል ውስጥም እነዚህ ይጠቀሳሉ

- ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ አንድ ኃይል አለ ያ ኃይል ግን ከዓለም የተለየ ፍጹም ልዑል ከፍጥረቱ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የማይታወቅ ከእውቀት በላይ የሆነ የማይናገር ስለእርሱ ሊነገርለት የማይቻል ነው፡፡

- ዓለምን የሚያስተዳድሩ ሁለት አማልክት አሉ ብለው ያስተምራሉ አንደኛው አምላክ ጨለማን በዓለም ላይ የሚገኙ ክፉ ነገሮችን የፈጠረ ሲሆን ሌላኛው አምላክ ደግሞ ብርሃንና ፀሐይን መልካም ነገሮችን የፈጠረ ነው ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡

ይህ የፍልስፍና ትምህርት በምዕራቡ ዓለም ሁሉ የተስፋፋ ሲሆን በኋላም በሮማውያን የቅኝ ግዛት ዘመን ወደ መካከለኛው ምስራቅና ሌሎች ሀገሮችም ቦታ ሊያገኝ በቅቷል በአጠቃላይ ይህ የፍልስፍና አስተምህሮ በሕዝቡ ዘንድ ዘልቆ ከመግባቱም ባሻገር ከዚህ ውጭ የሆነ እምነት ያለው ሁሉ እንዳላዋቂ ይቆጠር ነበር፡፡ ዘመናዊ ለመባልም ማንኛውም ሰው ወደ ፍልስፍና ትምህርት ቤቶች መግባት ግዴታው ነበር፡፡
ቅድስት ቤተክርስቲያን ግን እግዚአብሔር አምላክ ከፍጥረቱ የተለየበት ጊዜ እንዳልነበረና የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ እርሱ ብቻ እንደሆነ ታስተምራለች ይህንንም ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ፡፡ ይህን ዓይነት የክርስትና አስተምህሮ በፍልስፍና ተጠበብን ለሚሉ ሰዎች ለመቀበል እጅግ አስቸጋሪ ሆኖባቸው ነበር የክርስትና ትምህርት የተጀመረው ከፈላስፋዎቹ ሀገር ከግሪክ ወይም ከሮም ባለመሆኑ አልተቀበሉትም ነበር ሆኖም ግን ከአህዛባና ከቤተ አይሁድ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የገቡ ብዙ በመሆናቸውና ትምህርቱም ልብን የሚነካና የዘላለም ሕይወትን የሚሰጥ በመሆኑ ወደ ሃይማኖቱ ሊገቡ ችለዋል ሆኖም ወደ እምነቱ ከመጡ በኋላ ትልቁ ጥረታቸው የክርስትናን ትምህርት ከፍልስፍና ጋር ለማስታረቅ ነበር ምክንያታቸውም፡-

- የግሪኮች ፍልስፍና በክርስትና ተበልጦ ማየት ስለማይፈልጉ

- ማንኛውም አስተምህሮ ከፍልስፍና የተቀዳ ነው በኋላም የዳበረ ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡

ከዚህ የተነሳ ብዙ የፍልስፍና አስተሳሰብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዘልቆ በመግባት ችግር ሲፈጥር ታይቷል ኋላም ለቤተ ክርስቲያን መከፋፈልና ሌሎች እምነቶች መፈጠር ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል

### ❖ የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ጠላቶች

የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ጠላቶች በየጊዜው የተነሱ ብዙ ቢሆኑም ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን እንመለከታለን

- ✓ ቢጽ ሐሳውያን

ቢጽ ሐሳውያን የሚባሉት በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ሲሆን ሃሰተኛ ወንድሞች ይባላሉ፡፡ እነዚህ መናፍቃን ከአይሁድ ወገን ክርስትናን የተቀበሉ ሲሆን ካመኑና ከተጠመቁ በኋላ ተመልሰው ወደ አይሁድ ሃይማኖት ያዘነበሉ ናቸው፡፡ ከአህዛብ ወገን ክርስትና የተቀበሉትን አስቀድማችሁ የአይሁድን ሃይማኖትና የረበናትን ልማድ ያዙ ጥምቀት ያለግዝረት ክርስቶስ ያለ ሙሴ ወንጌል ያለ ኦሪት አይጠቅማችሁም እያሉ ያውኳቸው ነበር፡፡ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ውስጥ በ50 ዓ.ም በተደረገ የሐዋርያት ጉባኤ (የመጀመሪያው ሲኖዶስ) ይህ ትምህርት የተሳሳተ መሆኑ በግልጽ ተበይኗል፡፡

- ✓ ግኖስቲኮች

ግኖስቲኮች ማለት አዋቂዎች (የእውቀት ሰዎች) ማለት ነው፡፡ የቃሉን ትርጉም የወሰዱት “ግኖሲስ” እውቀት ከሚለው የጽርዕ ቋንቋ ነው፡፡ትምህርታቸውም ግኖስሲቲዝም ይባላል፡፡ እውቀታዊ ማለት ሲሆን መዳን በእውቀት ብቻ እጂ በእምነት አይደለም የሚሉ ነበሩ፡፡ ግኖስቲኮች ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ የክርስትና እምነት በዘመናቸው ከነበረው ፍልስፍና፣ ጥንቆላ፣ የምትሀት ትምህርት ጋር ይቀላቅሉ ነበር፡፡ ይህ የሐሰት ትምህርት የተጀመረው በሶሪያ(አንጾኪያ) በግብፁ(እስክንድርያ) በታናሿ እስያ ነበረ፡፡ ሁሉም ከተሞች በሮም ግዛት ውስጥ ነበሩ፡፡ ግኖስቲኮች የአይሁድን በዓልን ከግሪኮች ፍልስፍና ጋር የቀላቀለውን በሁለት አማልክት ማምለክ መመሪያ አድገው ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡ ከአስተምሯቸውም መካከል

- ስለ አምላክ የግኖስቲኮች ትምህርት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ ሳይኖራቸው ፈጣሪ ከፍጡሩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም እንዲሁም ክፍና ደግ አምላክ የተባሉ ሁለት አማልክት እንዳሉ ያስተምራሉ፡፡ ብርሃንን፣ ፀሐይን ሐዲስ ኪዳንን የፈጠረ ደጉ አምላክ ሲሆን፤ ጨለማን ብሉይ ኪዳንን የፈጠረ ደግሞ ክፉ አምላክ ነው ብለው ያስተምራሉ፡፡

- ስለ ሥነ ፍጥረት የግኖስቲኮች ትምህርት

ይህ ዓለም በክፉ አምላክ የተፈጠረ ስለሆነ የኃጢአት ምንጭ ነው ብለው ያምናሉ። ስለ ዓለም አፈጣጠርም ሲናገሩ በባህርይ መለኮቱ እደ እሳት ነበልባል ክፋይ ከሚወጡ ነገሮች ሲሆን እነዚህ ነገሮች እየራቁ በሄዱ መጠን ፍፁምነታቸው እየቀነሰ ይሄዳል። ከእነዚህ ነገሮች አንዱ ተሳስቶ ከመስመር ወጣ ስለዚህ ወደዚህ ዓለም ተጣለ። ይህ የተሳሳተና የተጣለው ሰውንና ቁሳዊ ዓለም ፈጠረ ይላሉ። የክርስቶስም አመጣጥ እንደዚሁ ነው ብለው ያምናሉ።

- ስለ ሰው ተፈጥሮ የግኖስቲኮች አስተሣሠብ

ግኖስቲኮች ሰው በመባል የሚታወቀውና ሰብዓዊ ክብርም ያለው ነፍስ እንጂ ስጋ አይደለም። ይህች የሰው ነፍስም እንደ እሳት ነበልባል ክፋይ ከመለኮት ባህርይ እየተከፈለች የምትወጣ ናት። የመዳን ተስፋ ያላት ነፍስ ብቻ ናት። ሥጋ በባህርይው ለጥፋት የተፈጠረ ስለሆነ ፈርሶ በስብሶ ይቀራል። ነፍስ በመዋቲ ስጋ ውስጥ በእድል ሰንሰለት ተጠፍራ (ታስራ) ትኖራለች። ከዚህ እስራት ሊፈታት የሚችለው እውቀት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ግኖስቲኮች ሰውን በሦስት ደረጃዎች ይከፍሉታል

- ❖ መንፈሳዊ
- ❖ ነፍሳዊና
- ❖ ሥጋዊ ናቸው

- ➢ መንፈሳዊ፡ የሚሉት እራሳቸውን ነው። ደረጃውም የፍፁምነት ነው። በእውቀታችን አስቀድመን ድነናል ባዮች ናቸው።
- ➢ ነፍሳዊ፡- የሚሉት ክርስቲያኖችን ነው። ደረጃው የማዕላዊነትና የወጣኒነት ነው። እነዚህ በመዳንና በመጥፋት መካከል ያሉ ናቸው። ቢያውቁ ይድናሉ ያለዚያ ግን ተስፋ የላቸውም ይላሉ።
- ➢ ሥጋዊ፡- የሚሉት አህዛብንና አይሁድን ነው። እነዚህ ለጥፋት የተፈጠሩና ተስፋ የሌላቸው ናቸው ብለው ያምናሉ።

በግኖስቲኮች እምነት ነፍስ ከሥጋ በምትለይበት ጊዜ ሥጋ በስብሶ ሲቀር ነፍስ ወደ ቀደመ ባህሪዋ ትመለሳለች ብለው ያምናሉ።

- ግኖስቲኮች ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ያላቸው አመለካከት

ግኖስቲኮች በምሥጢረ ሥጋዌ(ተዋህዶ) ትምህርታቸው ሥጋ የኃጢአት ምንጭ ስለሆነ ከመለኮት ጋር አልተዋሀደም ብለው ያምናሉ። ስለዚህ መለኮታዊ ቃል ሥጋ የለበሰ መስሎ ታየ ብለው ያስተምራሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ የዮሴፍ ልጅ እንጂ በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና አልተወለደም ይላሉ። በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ጀምሮ እስከ ስቅለት ድረስ ተዋህደው ድህነትም የሚገኘው ክርስቶስ ባደረገው ሥራ ሳይሆን በእርሱ በተገለጠው እውቀት ነው ይላሉ። የማስተማር ስራውን ጨርሶ ወደ መስቀል በሚወጣበት ጊዜ ከእርሱ ተለይቶ ሄደ ኢየሱስ ብቻውን መከራ ተቀበለ ብለው ያስተምራሉ። በዚህም ትምህርታቸው እስከ 3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያንን ሲያውኳት ኖረዋል።
የግኖስቲኮችን ስምና የተዘበራረቀ ትምህርታቸውን በሙሉ ለመጥቀስ አስፈላጊ ባይሆንም ዋና ዋናዎቹን ስምና ከትምህርታቸውም በመጠኑ እንመለከታለን።

### 1.ሲሞን መሠሪ

በሰሜን ፍልስጤም በሰማርያ ግዛት በጥንቆላ ሥራው ይተዳደር የነበረ ታሪኩ በሐዋርያት ሥራ 8፡13-24 የተጠቀሰው ነው። ከጥንቆላውና ከምህታቱ ጋር የሚስማሙ የግኖስቲኮችን ትምህርቶች በማጥናትና ትምህርቱንም ያስፋፋ የመጀመሪያው መናፍቅ ነው። ለዚህም የቤተክርስቲን አባቶች ርዕሰ መናፍቃን ብለውታል። የሲሞን መሠሪ አስተሳሰብና አስተምህሮውም

- ➢ ሁሉን የፈጠረ ሁሉን የመደምሰስ ኃይል ያለው እሳት ነው። እሳት የሚታይና የማይታይ ሁለት ባህርይ አለው። የሚታየው የሚታየውን ዓለም ይገዛል። የማይታየው እረቂቁን ይገዛል ይላል።

- ስለ እራሱ አመጣጥም ሲገልጽ በሰማርያ እንደ አብ፣ በይሁዳ እንደ ወልድ፣ በአህዛብ ዘንድ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሆኜ የታየሁና የተገለጥኩ መሲ ክርስቶ እኔ ነኝ እያለ የምንታዌ (የሁለትነት) ትምህርት ያስተምር ነበር፡፡
- ስለ ዓለም አፈጣጠርም ሲናገር ይህ ዓለም የተፈጠረው ሰው በስህተቱ ከፈጣሪው ከተጣላ በኋላ ነው ይላል፡፡
- ሁለት አማልክት አሉ ብሎ ስለሚያምን ይህ ዓለም የተፈጠረው በዝቅተኛው(በተዋራጁ) አምላክ ነው ይላል፡፡

ስምዖን መሠሪ በ53 ዓ.ም በሮም ውስጥ ሞቷል፡፡ አሟሟቱም እኔ ክርስቶስ ነኝ እያለ የክርስቶስን እድገት በማስመሰል በምትሃት ወደላይ ከፍ እያለ ሲሄድ ቅዱስ ጴጥሮስ በትምህርተ መስቀል ቢያማትብ ወደ ላይ ያነሱት አጋንንት ስለራቁ ወድቆ እንደሞተ የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡

**2.መርቅያን**

በታናሻ እስያ ግዛት ውስጥ የተወለደ ሲሆን አባቱም ኤጲስ ቆጶስ ነበር፡፡ መርቅያን በልጅነቱ ወራት በቤተክርስቲያን በፈፀመው ጥፋት ከቤተክርስቲያን አባረውታል፡፡ በ105 ዓ.ም ወደ ሮም ግዛት በመምጣት ለድሆች ምጽዋትን በመስጠት ተቀባይነትን አገኘ እንዲሁም ከመናፍቃን ጋር እየተከራከርኩ ነው በሚል ሽፋን የራሱን ንፋቄ ይዘራ ስለነበር ከቤተክርስቲያን በድጋሚ ተባሯል፡፡ የመርቅያን አስተሳሰብና አስተምህሮ

- መርቅያን ሁለት አማልክት(ክፉና ደግ) የሚለውን ሃሳብ ይደግፋል፡፡ ከግኖስቲኮች የሚለይበት ነገር ቢኖር ክፍ አምላክ ከደጉ አምላክ የተከፈለ አይደለም፡፡
- መርቅያን በክፋት የሚጠራውና የሚያማርረው የእስራኤልን አምላክ ነው፡፡ ክፉ አምላክ በብሉይ ኪዳን ሲሠራ ሲቀጣ የኖረ ጨካኝ ዳኛ ነው፡፡ ምህረትና ርህራሄ የለውም ይላል ደጉ አምላክ ግን ክርስቶስ እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ ማንም የማያውቀው ተሰውሮ የኖረ ክርስቶስ ስለ እርሱ መጥቶ አስተማረ ሐዲስ ኪዳንንም ሠራ ህዝቡንም ከክፉ አምላክ አላቀቀ ብሎ ያስምራል፡፡
- የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ምትሀት እንጂ አማናዊ አይደለም ብሎ ያስብ ነበር
- ክርስቶስ በመስቀል የተቀበለው መከራ በምትሃት ስለሆነ እርሱን አላገኘም ባይ ነው፡፡
- መርቅያን ጿሚና ታራሚ ስለሆነ የሚከተሉትን ጾምን እንዲያዘወትሩ አጥብቆ ያስተምር ነበር፡፡ ይህም አስተምህሮ ቶሎ ከሥጋ ለመላቀቅና ከዚህ ዓለም ፈጣሪ ለመላቀቅ ነው፡፡
- የብሉይ ኪዳንን ህግ አብዝቶ ስለሚጠላ በቀዳሚት ሠንበት የጾምና የሀዘን ቀን እዲሆን አዟል፡፡
- ጋብቻንም አብዝቶ ይቃወም ነበር የሚያጠምቃቸውም ያላገቡትንና ከሴት ርቀው ንጽህና ተብቀው የሚገኙትን ነው፡፡

**❖ ሁለቱ የትርጓሜ ትምህርት ቤቶች**

ቅዱሳት ሐዋርያት ከጌታ የተቀበሉት (የተማሩት) በሚገባ ለማስተላለፍ ከረዳቸው ነገር አንዱ ትምህርት ቤት ማቋቋማቸው ነበር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቀው የመጀመሪያው ትምህርት ቤት በ80 ዓ.ም በቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ የተመሰረተው የእስክንድርያ ትምህርት ቤት ነው የትምህርት ቤቱ ዓላማም አዳዲስ አማኞች በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት በማሰልጠንና ከዚያም ሲወጡ ወገኖቻቸውን ለማስተማር የሚያስችላቸውን እውቀት እንዲያውቁ ማድረግ ነው በ2ኛውና በ3ኛው ክፍለ ዘመን ከመንፈሳዊ እውቀት ባሻገር ሁለገብ ዕውቀትና ፍልስፍናም ጭምር ይማሩ ነበር፡፡

ሁለተኛው ትምህርት ቤት በሶርያ ዋና ከተማ በነበረው በአንጾኪ ተመሠረተ፡፡ ይህን ትምህርት ቤት የመሠረተው ሉቂያኖስ የተባለው ሰው ነው ትምህርት ቤቱም የተመሠረተው በ3ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ሲሆን በዚህ ትምህርት ቤት ብዙ ፈላስፎች ገብተው ተምረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የፍልስፍናው አስተሳሰብ የክርስትናውን እምነትና ትምህርት በክሎታል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ፍልስፍና በጣም ነግሶ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

**➢ የእስክንድር የትርጓሜ ትምህርት ቤት**

በዚህች ከተማ ብዙ የግሪክና የግብፅ ፈላስፎች የጥበብ ሰዎች ስለነበሩ ክርስቲያኖችም እምነታቸውን ለማስተዋወቅና የጥበብና የፍልስፍና ሰዎችን ለመምረጥ ሲሉ ትምህርት ቤቱን በእስክንድርያ መስርተዋል፡፡ ብዙ ታላላቅ ፈላስፎችና የፍልስፍና

ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ቤት አማካኝነት ክርስቲያን ሆነዋል፡፡

➢ **የአንጾኪያ ትርጓሜ ትምህርት ቤት**

በሐዲስ ኪዳን ታሪክ ውስጥ ከአህዛብነት ወደ ክርስትና የተመለሱ ክርስቲያኖች ዝነኛ መናኸሪያ ስለነበረች (አርድእት) የሚለውን ስያሜ ተለውጦ ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የሚለውን ስያሜ ያገኙት በአንጾኪ ከተማ ነው፡፡

የሁለቱ ትምህርት ቤቶች መመሥረት በክርስትና ትምህርት አያሌ ሊቃውንትን አስገኝቷል በአንፃሩ ደግሞ በፍልስፍናው ተጽእኖ ብዙ ወገኖች ኢ-ክርስቲያናዊ በሆነ ሥጋዊ አስተሳሰብ ተመርዘው ጠፍተዋል፡፡ሁለቱ ትምህርት ቤቶች በትርጓሜ ትምህርት አሰጣጣቸውም የተለያዩ ነበር፡፡ የእስክንድርያ ትምህርት ቤት ንባብ ይገላል ትርጓሜ ያድናል በሚል ቃለ እግዚአብሔር መሠረት ቅዱሳን መጻሕፍትን በአንድምታ ትርጓሜ ሲተረጉሙ የአንጾኪያ ትምህርት ቤት ደግሞ ገፀ ንባቡን በነጠላ ትርጓሜ ብቻ ይተረጉሙ ነበር፡፡ በዚህም ይነቃቀፉ ነበር፡፡

❖ ***የመናፍቃን መነሳትና ዓለም አቀፍ ጉባኤያት***

በቤተክርስቲያን ታሪክ የብዙዎች መናፍቃን ችግራቸው የፍልስፍናውን አስተሳሰብ ከክርስትናው ጋር ለመቀላቀል በመሞከራቸው ነው፡፡ ጌታችን ለድኅነተ ዓለም ሲል ሰው ሆነ በላ፣ ጠጣ፣ ደከመው በፈቃዱ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፤ ስጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ እንድንበት ዘንድ ሰጠን የሚለው የክርስትና ትምህርት ከፍልስፍናው ዓለም ለመጡት አምነው ለመቀበል እጅግ ያስቸግራቸው ነበር፡፡ ለውድቀትም ተዳርገዋል፡፡ ከእዚህ መናፍቃን የተወሰኑትን እንመለከታለን፡፡

**1.ቀለሜንጦስ ዘእስክንድሪያ**

ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ትምህርት ቤት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ የሐዋርያት አባቶች ድርሳናትን ምእዳንን አጥንቷል፡፡ ከቅዱስ ዲሜጥሮስም ስልጣነ ክህነትን ተቀብሏል፡፡ በተማረበት ትምህርት ቤትም ለ10 ዓመታት አስተሯል፡፡
ቀለምንጦስ የግሪኮችን ፍልስፍና እያጠና ስላደገ በእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መምህር በነበረበት ጊዜ ያስቸግር ነበር፡፡

የቀለሜንጦስ አስተምህሮ

- ቀለሜንጦስ እውቀትና እምነትን ይቀላቅል ነበር፡፡
- እግዚብሔርን ከፍጥሩ የተለየ አድርጎ ይገምት ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ወልድን ከአብ ጋር እያስተካከለ አንዳንዴም ያሳንሰው ነበር
- መዳን የሚገኘው በፍፁም እውቀት ነው ብሎ ያምን ነበር

**2. አርጌንስ**

አርጌንስ የተወለደው በእስክንድርያ ሲሆን እናትና አባቱም ክርስቲያን ነበሩ፡፡ አርጌንስ የመጀመሪያ ትምህርቱን የተማረው በእስክንድርያ ሲሆን ያስተማረው መምህርም ቀለሜንጦስ ነው፡፡ ቀለሜንጦስ የእስክንድርያን ትምህርት ቤት ለቆ በተሰደደ ጊዜ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ዲሜጥሮስ የ17 ዓመቱን አርጌንስን በመምህሩ ተተክቶ እንዲያስተምር ሾመው፡፡ አርጌንስ ለ30 ዓመታት ያህል አገልግሏል፡፡ በእስክንድርያ ከተማ ከነበረው የፍልስፍና ትምህርት ቤት ገብቶ የፕላቶን ፍልስፍና ከአሞንዮስ ተምሯል፡፡ በ231 ዓ.ም ለቀ ጳጳሱ ድሜጥሮስ ለቤተክርስቲያን ጉዳይ ወደ ጽርዕ ላከው አርጌንስ ግን ወደ ቂሳርያና ፍልስጤም ጉዞውን አደረገ ወዳጆቹ ከነበሩት ከኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶሳት እስክንድሮስና ቲዎክቲቶስ ዘንድ የቅስና ማዕረግን ተቀበለ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ይሄን በሰማ ጊዜ የሰበካ ክልልን በመጣስ የተሰጠ ህገ ወጥ ክህነት ስለሆነ የሾሙትንም ተሿሚውንም አውግዞታል፡፡

የአርጌንስ ትምህርት እንደ መምህሩ ቀለሜንጦስ የክርስትናን እምነት ከእውቀት ጋር ለመቀላቀል የሞከረ ሰው ነው፡፡ አርጌንስን ለውግዘት ያበቃው ፕላቶናዊ ትምህርቱ ነው፡፡ ትምህርቱ በሙሉ የፕላቶና የቀለሜንጦስ ነበረ፡፡
አርጌንስ ብዙ መጻሕፍትን የጻፈ ቢሆንም የእግዚአብሔር ምህረት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለፍጥረቱ ሁሉ አጋንንትንም ጭምር የሚጠቃልል ነው ይላል፡፡ ይህም ትምህርቱ በእስክንድርያና በአንጾኪ ሲጪቃጭቅ ከቆየ በኋላ በቆስጠንጥኒያ በተደረገ ጉባኤ እርሱ እና ትምህርቱ ከነመጻሕፍቱ ተወግዘዋል፡፡

**3. ሰባልዮስ**

ሰባልዮስ በሮም እግዚአብሔር አንድ ገጽ አንድ አካል ነው የሚለውን ትምህርት የተማረ ሲሆን አብ መከራን ተቀበለ ከሚሉ መናፍቃን ነው፡፡ እነዚህ መናፍቃን በሮም ያስተምሩት የነበረው ሞዴሊስቲክ ሞናርኪያኒዝም ይባላል፡፡ ሰባልዮስ ይህን የክህደት

ትምህርት ይዞ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የኑፋቄ ትምህርት ማስተማር ጀመረ። በሰባልዮስ አስተሳሰብ አንዱ አካል አብ በብሉይ ኪዳን አብ፣ በዘመነ ሥጋዌ ወልድ በበዓለ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ተባለ እንጂ አንዱ አካል ነው ብሎ ያምንና ያስተምር ነበር።

**4. ጳውሎስ ሳምሳጢ**

የተወለደው ታናሿ እስያ በሶሪያ አካባቢ ሲሆን ሳምሳጢ የተባለው በሀገረ ስብከቱ ነው። አስተምህሮውም እንደ ሰባልዮስ አንድ ገጽ እያለ ነው። የጳውሎስ ሳምሳጢ የክህደት ትምህርት ዳይናሚክ ሞናርኪዝም ይባላል። ቃል አካል ሳይኖረው በአብ አካል ውስጥ የኖረ ኃይል ነው ማለት ነው። ሌላው ትምህርቱ ከማርያም የተወለደው እሩቅ ብእሲ ነው ስሙም ኢየሱስ ይባላል። ኢየሱስ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ በአብ ህልውና ውስጥ የነበረው ዝርው ቃል መጥቶ አደረበት ከዚያ በኋላ በሠራው ተጋድሎ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል በቃ በማለት የክህደት ትምህርት ያስተምር ነበር። ጳውሎስ ሳምሳጢን ከግኖስቲኮች በወረሰው የህድረት ትምህርቱ ቤተክርስቲያንን ስላናጋ የቃልን በቅድምና መኖር (የአካልን ከዊን) በኋላም በሥጋ መምጣቱን በአማናዊ ተዋህዶ ሰው መሆኑን ሥጋ መልበሱን ስለካደ 268 ዓ.ም በአንጾኪያ ጉባኤ ተደርጎ እርሱም ትምህርቱም ተወግዟል። አባቶቻችን የጳውሎስ ሳምሰጢን ትምህርት አምነው የተጠመቁ ቢኖሩ እንደገና እንዲጠመቁ ሠለስቱ ምዕት በቀኖናቸው ወስነዋል።

**5. ሉቂያኖስ**

ሉቂያኖስ የአንጾኪያን ትምህርት ቤት የመሠረተና ለረዥም ጊዜም ያስተማረ ነው። የግኖስቲኮችን የፍልስፍና ትምህርት አራማጅ ከመሆኑም ባሻገር በቅድምና የነበረው ቃል (ወልድ) ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት በስልጣን አንድ መሆኑን አይቀበልም ነበር።

የአንጾኪያ ተማሪዎች ብዙዎቹ የማይታመኑበትም ምክንያት ት/ቤቱን የመሠረተው ሉቂያኖስ የጳውሎስ ሳምሳጢን ደጋፊ በመሆኑና መናፍቅ ስለሆነ ነው። የእስክንድርያው ት/ቤት ምሁር እለስክንድሮስ ሊቂያኖስን የጳውሎስ ሳምሳጢ አልጋ ወራሽ ሲለው የቆጵሮሱ ሊቀጳጳስ ኤጲፋኒዮስም መርዝ የተቀባ ነው ሲል በጽሑፉ ገልጾታል።

**6. አርዮስ**

አርዮስ በ257 ዓ.ም ገደማ በሰሜን አፍሪካ ሊቢያ የተወለደ ሲሆን በአንጾኪያ ት/ቤት ከተማሩና የቤተክርስቲያንን ትምህርት ወደ ፍልስፍና ሊመልሱ ከሞከሩት አንዱ ነው። አርዮስ ከቤተክርስቲያን ጋር ያጣላው ትምህርት የወረሰው ከሉቂያኖስ ነው። ወደ አንጾኪያ ከመሄዱ በፊት በእስክንድርያ እንደተማረ ይነገራል። በአንጾኪያ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ወደ እስክንድራያ ተመልሶ መኖሪያውን እዛው አድርጓል። የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ ከነበረው ከተፍፃሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ የዲቁና መዓረግ ተቀብሏል። የዲቁና ማዕረግ ከተቀበለ በኋላ በውስጡ ያለውን ማንነቱ(ምንፍቅናውን) በማውጣት ማስተማር በመጀመሩ ቅዱስ ጴጥሮስ ከቤተክርስቲያን አውግዞ ለይቶታል። ቅዱስ ጴጥሮስ ካረፈ በኋላ አኪላስ ተሾመ። አኪላስም የአባቱን አደራ ጥሶ ከእስሩ ፈቶታል። በዚህም በዓመቱ ተቀስፎ ሞቷል። እለእስክንድሮስ ከተሾመ ቦኋላ በድጋሚ አውግዞታል።

አርዮስ ሲያስተምር ግጥም በመግጠም ድርሰት በመድረስ የሰዎችን ልብ እያማለለ ስለነበረ ብዙ ወዳጆችን ለማፍራት ችሏል። አርዮስ የተለያዩ አባቶች ሊቀ መናፍቃን ይሉታል። ይህንንም ያሉበት ምክንያት የጳውሎስ ሳምሳጢንን፣ የአርጌንስን፣ የሉቂያኖስን አስተሳሰብ ያጠቃለለ አስተምህሮ ስለነበረ ነው።

**የአርዮስ አስተምህሮ**

- እግዚአብሔር ፈጣሪ እንጂ ወላዲነት የለውም፤ ቀዳሚ የሌለው አብ ብቻ ነው ከእርሱ በቀር ሁሉ የተፈጠረ ነው
- በምሥጢረ ሥላሴ አብ አባት ተብሎ የተጠራው በአባትነትም የታወቀው ከዘመናት በኋላ እንጂ ከዘመናት በፊት አይባልም።
- አብ በራሱ ፈቃደ ዓለምን ለመፍጠር ስላሰበ መስፈሪያና መለኪያ እንዲሆነው ሌላ ጥበብ(ወልድን) ፈጠረ ብሎ ያስባል።
- በመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ፣ ወልድ፣ ቃል በባህርይው ፍጡር ስለሆነ ያልነበረበት ጊዜ ነበረ።
- ወልድ ለአብ የመጀመሪያው ፍጥረቱ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም ለወልድ የመጀመሪያ ፍጥረት ነው።

አርዮስ ትምህርቱ በፍልስፍና ብቻ ሳይሆን በቅዱሳት መጻሕፍትም የተመሠረተ ነው ለማስባል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይጠቅስ ነበር። ይጠቅስ ከነበረው ምሳ 8-22 "ጥበብ ከፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ እኔን ፈጠረችኝ" የሚል ገጸ ንባብ እንደ እርሱ አተረጓጎም ጥበብ የተባለው ወልድ ነው። ፈጠረኝ ማለቱም እግዚአብሔር አብ ፈጠረኝ ማለት ነው በማለት የክህደት ትምህርቱን ያስተምር ነበር።

- **ዓለም አቀፍ የቤተክርስቲያን ጉባኤያት**

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀዳሚና ተቀባይነት ያላቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንም የምትቀበላቸው አበይት ጉባኤያት 3 ናቸው፡፡ እነርሱም

1. **ጉባኤ ኒቅያ**
2. **ጉባኤ ቁስጥንጥንያ**
3. **ጉባኤ ኤፌሶን**

**1.ጉባኤ ኒቅያ** ኒቅያ በጥቁር ባህር ወደብ አካባቢ የምትገኝ ስትሆን የተመሠረተችውም በዲዮናሲዮስ ነው፡፡ አርዮስ የተባለው መናፍቅ በተፍፃሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ተወግዞ የተለየ ሲሆን በአኪላስ ከውግዘቱ የተፈታ ሲሆን በኋላም በእለእስክንድሮስ ቢመከር አሻፈረኝ በማለቱ ወደ አንድ መቶ የሚጠጉ የሊቢያና የእስክንድሪያን ኤጲስ ቆጶሳት ሰብስቦ በ320ዓ.ም ምንፍቅና በጀመረ በ2ት አመቱ አውግዞ ለይተውታል አርዮስ ሲወገዝ የቀድሞ ጓደኛው የነበረው የኒቆሜድያ ኤጲስ ቆጶስ አውሳቢዮስ ሰብስቦ አርዮስ ከእስክንድርያ የተባረረው በግፍ ነውና ከውግዘቱ ፈተነዋል ብለው ተናገሩ፡፡ ይህንን ጉባኤ የመራው እራሱ አውሳብዮስ ነበረ፡፡ በ322 ዓ.ም አርዮስ ወደ እስክንድርያ በመመለስ እለእስከንድሮስ ቢያወግዘኝ ተፈትቼ መጣሁ በማለት በማን አለብኝነት የክህደት ትምህርቱን ማስተማር ቀጠለ ብዙ ተከታዮችንም አፈራ፡፡ ይህን አለመግባባት ሥር በመስደዱ ቆስጠንጢኖስ የእስፓኝ ጳጳስ ሆስዮስ ወደ እስክንድርያ ልኮ ነገሩን እንዲያጣራ ካደረገ በኋላ ጠቡ የሃይማኖት እንጂ የስልጣን አለመሆኑን በተረዳ ጊዜ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ እንዲደረግ አዋጅ አስነገረ፡፡ ጉባኤው በመጀመሪያ በእንቆራ ነበር ሊካሄድ የታሰበው ባልታወቀ ምክንያት ወደ ኒቂያ ተዘዋውሯል፡፡ በአዋጁ መሠረትም ብዙ ኤጲስ ቆጶሳትንና ሊቃውንት በኒቂያ ተሰብስበዋል፡፡ በጉባኤው ላይ ወልድ ዋህድ በማለት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው የተገኙት 318ቱ ሊቃውንት ብቻ ነበሩ ቤተክርስቲያንም ይህንን ቁጥር ትቀበለዋለች፡፡ ለፍትሐዊነት በጉባኤው የአርዮስ ደጋፊዎችም ተገኝተው ነበር፡፡ ጉባኤውን የመሩት ሊቀጳጳሳቱ እለእስክንድሮስ፣ ኤዎስጣቴዎስ እንዲሁም ኤጲ ቆጶሱ ሆሲዮስ ነበሩ፡፡ ለምዕመኑ አንድነት የመሰላቸውን እንዲያደርጉ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ሙሉ ስልጣን ሰቷቸዋል፡፡

- **ጉባኤው መጀመሪያ የተነጋገረባቸው አንቀጾች**

ሀ.አርዮስ ያቀረባቸው ሁሉንም ጥቅሶች መመርምር

ለ.ጥበብ የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጎመው ማየት

ሐ.ወልድ በባሕርይው ፍጡር ከሆነ በመዳን ምሥጢር ላይ ስለሚደርሰው አደጋ መወያየት

መ.የእግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጆች ሲል ወዶ ያደረገውን ተዋሕዶ አርዮስ የባሕርይ ተወራጅነት ቢኖርበት ነው ስለማለቱ

ሠ.ወልዱ በባሕርይ ፍጡር ሳለ እንደሌሎች ፍጡራን በገድል በትሩፋት የአምላክነት ክብር አገኘ ስለማለቱ፡፡

አርዮስ ከፍልስፍና ጋር በማዛመድ የሚመቸውን ጥቅስ በመጥቀስ ጥያቄ በመጠየቅ ሰጣ ገባ ውስጥ ሲገባ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ግን ጌታ አዳኝ መሆኑን መድኃኒትነቱም የባህርይ አምላክነትን የሚያስረዳ ነው፡፡ የሚያድንም እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ አስረዱ፡፡ ክርስቶስ አምላክ ካልሆነ አሁንም አልዳንም ማለት ነው፡፡ በእርሱ መዳናችንን ካመንን ግን ያዳነን እርሱ አምላክ መሆኑን ማወቅና ማመን አለብን፡፡ ፍጡር ፍጡርን አያድነውምና በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጌታ በገድል በትሩፋት አምላክ ስለሆነ ሊሰገድለት ይገባል ላለው ቅዱስ አትናቴዎስ ሲመልስ ፍጡር ከሆነና ለእርሱ የአምልኮ ስግደት የምንሰግድ ከሆነ አምልኮ በዓድ ነው ሲል ሀሳቡን ተቃውሞታል፡፡ ከዚህ ሁሉ ክርክርና መልስ በኋላ በጉባኤው የነበሩ አባቶች አትናቴዎስ እንዳቀረበው ከአብ ጋር አንድ ባሕርይ ነው በማለት የመለኮትን አንድነትና የአካል ሦስትነት የወልድን የባሕርይ አምላክነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ አንቀጸ ሃይማኖታቸው አጽድቀዋል፡፡ አርዮስንም አውግዘው ለይተውታል፡፡አሁንም በቤተክርስቲያን የሚሠራበት የሃይማኖት ቀኖና ይህ ነው፡፡ ይህም 12 አንቀጾች ያሉት ሲሆኑ 7ቱ በዚህ ጉባኤ የተረቀቁ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ይህ የኒቅያ ጉባኤ የተካሄደው በ325 ዓ.ም በ318 ተሰብሳቢዎች በተገኙበት በእለስክንድሮስ ሊቀመንበርነት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል በማረጋገጥ "ወልድ ፍጡር" ሲል የሳተውን ቀንደኛ መናፍቅ አርዮስን አውግዘው ለይተዋል፡፡

- **7ቱ አንቀጸ ሃይማኖት**

1.በአንድ አምላክ እናምናለን ሁሉን የያዘ አባት፣ ሁሉን የፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውንም

2. በእግዚአብሔር ልጅ በአንድ ክርስቶስም እናምናለን

3.ብቻውን ከአብ የተወለደ ይኸውም ከአባቱ ባሕርይ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተወለደ እውነተኛ

አምላክ፣ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ የሚሆን ሁሉ በእርሱ የሆነ
4. ታመመ፣ ሞተ ተቀበረ
5. በሦስተኛው ቀን የተነሳ
6. ወደ ሰማይ አረገ
7. ህያዋንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ ዳግመኛ የሚመጣ የሚሉት ናቸው፡፡

**2.ጉባኤ ቁስጥንጥንያ**

ጉባኤው የተካሄደው በ381 ዓ.ም በቁስጥንጥንያ ነው፡፡ ምክንያት የሆነ መቅዶኒዮስ መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው በማለት ባስተማረው ትምህርት ነው፡፡ ይህ ክህደት ሲነሳ የቁስጥንጥንያ ንጉስ የነበረው ቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ ይህ የቤተክርስቲያን ችግር በጉባኤ እንዲፈታ ባስተላለፈው መልእክት መሠረት 150 ሊቃውንት ተሰብስበዋል፡፡

በዚህ ጉባኤ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የተወያዩባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. መቅዶንዮስና ትምህርቱን ለማውገዝ
2.አቡሊናርዮስንና ትምህርቱን (በምሥጢረ ሥጋዌ ቃል እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሃደም የሚለውን ክህደት) ለማውገዝ
3.ወልድ የተዋሃደው የአዳምን ሥጋ አይደለም ሌላ በቅድምና የነበረ ሥጋ ነው እንጂ የሚሉ መናፍቃንን ለማውገዝ፡፡
4.በኒቅያ ጉባኤ ላይ በተረቀቀው ጸሎተ ሃይማኖት ላይ የተጨመሩ 5ቱን የሃይማኖት ቀኖናዎችን ማርቀቅ

በዚህ ጉባኤ ላይ መቅዶንዮስ መንፈስ ቅዱስ ሕፁጽ፣ ፍጡር ነው ያለበትን ምክንያት ሲጠየቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ከዚህም በኋላ ጉባኤው በኢሳይያስ 6-3፣ በማቴዎስ 28-19 በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድነትንና ሦስትነን በማስረዳት ቢነገረው ከኑፋቄው አልመለስም በማለቱ 150ው ሊቃውንት የክህደት ትምህርቱንና እርሱን አውግዘው ለይተውታል፡፡

ሌላው ጉባኤው የአቡሊናርዮስን በምሥጢረ ሥጋዌ ቃል እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሃደም የሚለውን የክህደት ትምህርት አውግዘዋል፡፡ ለዚህም በዮሐንስ 1-14 ላይ "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለውን በመጥቀስ በትክክል የቃልና የሥጋን ውህደትና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ሊቃውንት አስረድተዋል፡፡

ቅዱስ ጎርጎሪየስ ዘኢንዝናዙም ሰው ማለት ነፍስና ሥጋ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን እንጂ ነፍስ አልነሳም ከተባለ ያዳነው ሥጋን እንጂ ነፋስን አይደለም ብሎ በመመለስ የአቡሊናርዮስን ክህደት ተናግሯል፡፡ ከዚህም በማያያዝ ጉባኤው በኒቅያ ጉባኤ አንቀጸ ሃይማኖት ከተጠቀሱት ተጨማሪ 5 አንቀጾችን አስቀምጧል፡፡ እነርሱም

1. በጌታ በአዳኝ ከአብ በሠረፀ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፣ እንስገድለት እናመስግነው
2. በሁሉ ባለች በሐዋርያት ጉባኤ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡
3. ለኃጥያት ማስተሰርያ በምትሆን በአንዲት ጥምቀት እናምናለን
4. የሙታንን ትንሳኤ ተስፋ እናደርጋለን
5. የሚመጣውንም ሕይወት እንጠባበቃን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

**3.ጉባኤ ኤፌሶን**

ይህ ጉባኤ ሦስተኛው ዓለማቀፍ ጉባኤ ሲሆን ለጉባኤው መሰባሰብ ምክንያት የሆነው የንስጥሮስ የክህደት ትምህርት ነው፡፡ በምሥጢረ ሥጋዌ ክርስቶስን በሁለት ከፍሎ አንዱን የዳዊት ልጅ ሁለተኛውን የእግዚብሔር ልጅ ነው ብሎ ያምንና ያስተምር ነበር፡፡ ስለዚህ እመቤታችን የወለደችው የዳዊትን ልጅ እንጂ የእግዚብሔርን ልጅ አይደለም በማለት ያስተምር ነበር፡፡

ንስጥሮስ ለክህደት ትምህርቱ የተጠቀመበት ዮሐ 1-14 "ቃል ሥጋ ሆነ" የሚለውን መለወጥን ያስከትላል ያለውን ቃል በሥጋ አደረ ብሎ እንዲመቸው አድርጎ በመተርጎም መሪ ጥቅሱ ነበረ፡፡ ለንሥጥሮስ ለክህደት ትምህርቱ በሚገባ ምላሽ የሰጠው የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ ነው፡፡ ታላቁ አባት ቅዱስ ቄርሎስ የቃልና የሥጋን ተዋህዶ በማስረዳት የውላጤንና የኅድረትን ትምህርት ክህደቱን አጋልጧል፡፡ የንስጥሮስን ትምህርት በመጀመሪያ የተቃወመችው የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ነች የሚባለው በቅዱስ ቄርሎስ አማካኝነት ነው፡፡

**ምዕራፍ አምስት**

## የቤተክርስቲያን ታሪክ በዘመነ ፃድቃን

በዘመነ ፃድቃን የቤተክርስቲያን ታሪክ ምን እንደሚመስል ስናይ ብዙ ከሀድያን ተነስተው ቤተ ክርስቲያናን ሲያውኩ የነበረበት ዘመን ነው። በሃይማኖት፣ በፖለቲካ በሥልጣን ሽኩቻ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳደድ ሲሉ አባቶችና ብዙ ምዕመናን የተንገላቱበት ወቅትም ነው።
ሆኖም እግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በማመን የማይከፈል የማይለወጥ ባሕርይውን በመጠበቅና ጸንተው የቆሙ ሰዎች መጨረሻውን ድል የተጎናጸፉበት ቤተ ክርስቲያንን ወደ አንድነት የመለሱበት መናፍቃንን የረቱበት ጊዜ ነበር።

- **የቤተክርስቲያን መከፋፈል እስከ ፩ሺ፻፬ ዓ.ም**
- **ከኤፌሶን ጉባኤ በኋላ**

ከኤፌሶን በኋላ የተደረጉትን ጉባኤያት አምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉትም። ለ32 ዓመታት የእስክንድርያ መንበር ቅዱስ ቄርሎስ ከመራና ካገለገለ በኋላ በ440 ዓ.ም ሲያርፍ በመንበሩ ደቀመዝሙሩ ዲዮስቆሮስ 25ኛ የእስክንድርያ ፓትርክ ሆኖ ተሾመ።
ግብፃዊው ዲዮስቆሮስ ንስጥሮስን ለማውገዝ ወደ ኤፌሶን ሄዶ ነበር።እርሱም እንደ አትናቴዎስ ቄርሎስ ለሃይማኖቱ ቀናተኛ ነው። ባይሳካለችውም የታናሽ እስያ ግሪኮች በውዳሴ ከንቱ ጠልፈው ሊጥሉት ነበር። በዚሁ ጊዜ በቁስንጥንጥያ ውሳኔው የሚያስተምር አውጣኪ ተነሳ። የንስጥሮስን ስህተት የሸሸ መስሎት መለኮት ሥጋን ውጦታል፣ መጦታል በማለት ማስተማር መረጠ። ይህን መናፍቅ የቁስጥንጥያ ሊቀ ጳጳስ ፍላብያኖስ የሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶሳትን ብቻ ሰብስቦ በጉባኤው አወገዘው በቤተክርስቲያን ጉባኤ ባለመወገዙም ለቤተ መንግስት የክስ አቤቱታ አቀረበ። ንጉሱም አቤቱታውን ተቀብሎ በጉባኤ እንዲታይ ወደ ዲዮስቆሮስ ላከ እርሱም መልእክቱን ተቀብሎ ለስብሰባ ወደ ኤፌሶን መጣ። ስብሳቢውም ራሱ ነበር። የእርሱን ሰብሳቢነት የተቃወመ የሮማ ፓፓ ዘግይቶ ደረሰ። ፍላብያኖስም እርሱ ያወገዘው በጉባኤ በመታየቱ አልመጣም። ያም ሆነ ይህ ዲዮስቆሮስ የመጡትን 135 ኤጲስ ቆጶሳት ይዞ በእመቤታችን ቤተክርስቲያን ነሐሴ 8 ቀን በ449 በኤፌሶን ጉባኤ አደረገ። በጉባኤውም አውጣኪ የተወገዝኩት ንስጥሮስን በመቃወሜ በግል ጥላቻ ነው ብሎ ተናገረ። ዲዮስቆሮስም በሦስቱ ጉባኤያት የተወሰነውን ሃይማኖትና ቀኖና የሚሽር ሁሉ የተወገዘ ነው አለ። ልዮን የእርሱ መልእክተኞች ለጉባኤው ባለመገኘታቸው ጉባኤውን ጉባኤ ፊያት ብሎ ሰይመው ዲዮስቆሮስንም አወገዘው። አንዱ አካል ሁለት ባህርያት የሚለውን የኑፋቄ ትምህርቱን ለቁስንጥንጥንያው ፍላብያኖስ በቅፍና ፅፎ ላከለት በደብዳቤውም መከራን የተቀበለው ሥጋ፣ ተአምራት ያደረገው መለኮት መሆኑን በማተት ክርስቶስ ሁለት ባህርያት ሁለት ህላዌያት አንድ አካል እንደሆነ ገልጾ ጽፏል። ዲስቆሮስ ልዮን አፍላብኖስ የላከውን በሰማ ጊዜ ንስጥሮሳዊ ነህ ብሎ አውግዞታል።

አውጣኪ ለጊዜው ኦርቶዶክሳዊ ቢመስልም ቀስ በቀስ የውላጤ ትምህርቱን በቤተክርስቲያን ውስጥ ማስተማር ጀመረ። የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል የሆነው በተዋህዶ ሳይሆን በውላጤ ነው። መለኮተ ሥጋን ዋጠው መጠጠው እያለ ማስተማሩ በእስክንድርያ እንደተሰማ ዲዮስቆሮስ ወዲያውኑ አወገዘው።
ልዮንና ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ተወጋግዘው ባሉበት ሰዓት ንጉስ ቴዎዶስዮስ ከፈረስ ወድቆ በ450 ዓ.ም ሞተ። እኅቱም የአባቷን ጀነራል መርቅያንን አግብታ ነገሰች። ስማቸውንም ለማስጠራት በመቻኮል ከልዮን ጋር በደብዳቤ ከተነጋገሩ በኋላ ጉባኤ እንዲደረግ ተስማሙ። ጉባኤውም ጥቅምት 8 ቀን 451 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ። የጉባኤውም አላማ በቂ ምክንያት ባይኖረውም ከውጤቱ እንደምንረዳው የእስክንድርያ መንበርን ማቃለልና በጉባኤው የተወገዘውን የንስጥሮስን ትምህርት አዲስ የመሰየም ሐሳብ ነበረው። በተባለው ቀን 636 ሰዎች ተሰበሰቡ ጉባኤውን የመራው የልዮን እንደራሴ የቁስንጥንጥንያ ጳጳስ አንቶሊዮን ነበር።

ቅዱስ ዲስቆሮስም ከተቀመጠበት ተነስቶ አንድ ባህርይ ማለታችን ሁለቱን/እንደ አውጣኪ/ አጥፍተን አይደለም ወይም አንዱን ከሌላው /እንደ አቡሊናርዮስ/ ለውጠን ወይም አጣፍተን አይደለም።

ኑሰት፣ ሚጠት፣ ውላጤ የሚል በሙሉ የተወገዘ ይሁን እኛ የምንነቅፈው በንስጥሮስ ዘንድ ብቻ ነው ብሎ መንበሩን ላለማስደፈር ጉባኤውን ለቅቆ መጥቷል። በኤፌሶን በንስጥሮሳዊነታቸው የተወገዙት ቴዎድሪጦስና ኢማን በጉባኤው ሙሉ አባል ሆኑ። ጉባኤውም ንስጥሮሳዊ የተባለው ስለዚህ ነው። በመጀመሪያ በዚህ ጉባኤ የተወገዘው ዲዮስቆሮስ ነው። የተወገዘበትም ምክንያት ባለመስማማቱና ወደ ጉባኤው ለሁለተኛ ጊዜ ተጠርቶ ባለመምጣቱ እንደሆነ ተናግሯል። ንግስት ብርክልያ የጦማርን ደብዳቤ እንዲቀበል ብትጠይቀው እንቢ ስላላ ጢሙን አስነጭታ ጥርሱ እስኪወልቅ አስደበደበችው። እርሱም የወለቀ ጥርሱንና የተነጨ ጢሙን ለቤተክርስቲያን ልኮ ‹‹ የሃይማኖት ፍሬ ይህ ነው›› ብሎ ላከላቸው። መርቅያንም ወደ ጋግራ ደሴት እንዲጋዝ ወሰነ። እርሱም ጴጥሮስና ቴዎፒስቶስ የተባሉ ሁለቱን መነኮሳት ይዞ ተሰደደ።

ጉባኤው በልዮን ደብዳቤ ላይ ፈርሞ ለመለያየት ሲያስብ ንጉሱ አንድ ወጥ የሆነ ጋራ መግለጫ አሰሙ ስላላቸው ኮሚቴ

አቋቋሙ። ‹‹ክርስቶስ ከሁለት ባሕርይ የተገኘ ነው›› የሚለው የቄርሎስና የዲዮስቆሮስ ቃል ስለሆነ መውጣት አለበት ሲሉ መኳንንቱና ንጉሱ ተቃወሙ። ስለዚህ ኮሚቴው ይህን ሀሳብ ሰርዞ የሚከተሉትን አራት ነጥቦችን አርቅቆ ተፈራርመው ተለያዩ። እነርሱም፡-

፩. "አምላክ ፍጹም ወሰብእ ኅቡረ ህላዌ ምስለ አብ በመለኮቱ ኅቡረ ህላዌ ምስሌነ በትስብእቱ፡- ፍጹም አምላክ በአምላክነቱ ከአብ ጋር አንድ ነው። በሰውነቱ ከኛ ጋር አንድ ነው።"

፪. "እሙር በክልኤቱ ህላዌያት ዘእንበለ ፍልጠት ውላጤ ወቱስሕት፡- በሁለት ባህርያት የሚታወቅ ያለመለየት ያለመለወጥ ያለመቀላቀል።"

፫. "ወተዋሕዶ ኢያእተተ ፍልጠተ ማእከለ ክልኤቱ ሕላዌያት፡- ተዋሕዶው በሁለቱ ባህርያት መካከል ያለውን ልዩነት አላጠፋውም።"

፬. "ወሀብታተ ክልኤቱ ሕላዌያት ይትወቀቡ በበህላዌ ሆሙ ወእም ክልኤሙ ይትረከብ አሐዱ አካሉ፡- የሁለቱ ባህሕርያት ገንዘቦች በየባሕርያቸው ተጠብቀው ሁለቱም አንድ አካልን ያስገኛሉ።" የሚሉት ናቸው።

በምስራቃውያን ዘንድ ይህ ስብሰባ ጉባኤ አብዳን፣ ጉባኤ ከለባት /የውሾች ጉባኤ/ ይባላል። ጉባኤውንም የተቀበሉት መለካውን ይባላሉ። የንጉሥ ቃልን ትክክል ነው ብለው የሚቀበሉ የቤተ መንግስት ፊት አግቢዎች ውሾች መባላቸው ቤተክርስቲያንን ለቁስጥንጥንያ ነገስታት አሳልፈው ሰጥተዋልና ነው።

ዲዮስቆሮስ ከተጋዘ በኋላ ፕሮቴርዮስ የተባለ መለካዊ መነኩሴን ልዮንና መርቅያን በመመካከር የእስክንድርያ ፓትርያርክ አድርገው ቢሾመም ሕዝቡ ባለመቀበል አምጾ ነበር። በግርግሩም ፕሮቲርዮስ ሞተ በመካከሉም በ454 ዓ.ም የተዋሕዶ አርበኛው ዲስቆሮስ በግዞት ሳለ በማረፉ ሕዝቡ ጢሞቴዎስ የተባለውን አባት መርጠው ፓትርያርክ አድርገው ሾሙት። ሰላም በማጣት በብጥብጥ ላይ የነበረችው እስክንድርያም ተረጋጋች።

## ፃድቃንና ተጋድሎአቸው

"ፃድቃን" የሚለው ቃል ለሁሉም አይነት የክርስትና እምነት ቅዱሳን ሁሉ የሚሰጥ የወል መጠሪያ ቢሆንም ይህን ቃል በስምምነት ጭምር የሚጠሩበት ግን ከዚህ ዓለም ተድላ፣ ደስታ ርቀው፣ ዳዋ ጥሰው፣ ድምጸ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን ታግሰው፣ ጤዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ የላመ የጣመ ሳይቀምሱ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብሱ፣ እኖር ባይና እከብር ባይ ልቦና በሚያሰራው ኃጢአት ሰውነታቸውን ሳያሳድፉ የሚኖሩ ግልፅና ስውር መናንያን ናቸው።

ከክርስትና እምነት ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ምናኔ በእርግጥ በሐዋርያት፣ በሰማዕታት፣ በገዳማውያን ባህታውያን በዓለማውያን ምዕመናን ሕይወት የሚታይ ክርስቲያናዊ ጠባይ ስለሆነ ግድ ገዳማዊነት የሚጠይቅ ውሱን ገድል አይደለም። በምናኔ ሕይወታቸው በቤተክርስቲያን ታሪክ በአብነት ከሚጠቀሱት አበው አባ ጳውሊ፤ ቀጥሎም አባ እንጦንስ (250-356) አባ ጳኩሚስ አባ መቃርዮስ፣ አባ አሞን (290-346) የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያምና ሌሎችም ናቸው።

በአባ ጳውሊ የተጀመረው ምናኔ በአባ እንጦንስ አሁን ያለው የምንኩስና የገዳማዊ ኑሮ ይዘትና ቅርጽ እንዲኖረው ሲደረግ በአባ ጳኩሚስ ደግሞ ገዳማዊው የምናኔ ኑሮ እስከ አሁን ድረስ ጸንቶ ለመኖር ባበቃው ሥርዓተ ገዳም እንዲመራ ተደርጓል። ስለዚህም የምናኔ ሥርዓት በትክክል የተስፋፋበት ብዙ ቅዱሳን የምናኔን ሕይወት የፈጸሙበት ዘመን ስለነበር ዘመነ ፃድቃን ሊባል ችሏል።

- **የኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ**

የኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ስንል ምዕራባውያኑ ሳይሆን የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናትን ማለታችን ነው። እነዚህም አምስት ሲሆኑ በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

- **የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ**

ግብፅ የኮፕት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምንም እንኳ በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታይ በሆኑ በቢዛንታይን (በቁስጥንጥንያ) ነገሥታትና በእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑ ቅኝ ገዢዎች ቀንበር ሥር ለብዙ ዘመናት በመሰቃየት የምዕመኖቿ ቁጥር አሁን አንሶና ቀንሶ የምትገኝ ብትሆንም በ451 ዓ.ም እስከተደረገው እስከ ሴልቄዶን ጉባኤ ድረስ ግን ከሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በይበልጥ ለክርስትና እምነት መጠናከርና ለወንጌል መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች። ይኸውም በቅዱስ ማርቆስ ተመስርቶ ክርስቲያኑ ዓለም መጀመሪያ የነበረውን ዝነኛውን የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከፍታ በማስተማር ታላላቅ የቤተክርስቲያናት አባቶችንና ሊቃውንትን በማፍራት ለአለም ቃለ እግዚአብሔርን ስትመግብ ኖራለች።

እስክንድርያ አሁንም እምነቷ ሳይናወፅና ሳይቀላቀል ወይም ሳይበረዝ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነቷ ጸንታ ትገናለች። የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን በአሁን ጊዜ በከፍተኛ መንፈሳዊ ጥንካሬ ላይ የምትገኝ ሲሆን ከሀገሯ ውጭ በሱዳን፣ በኩየት፣

በደቡብ አፍሪካ፣ በዩ.ኤስ አሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውስትራሊያ፣ በኬንያ፣ ወዘተ አብያተ ክርስቲያናት መሥርታ ወንጌልን ታስተምራለች።

- **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስትናን በመንግስት ደረጃ የተቀበለው በ4ኛው መቶ ክ/ዘመን ቢሆንም በ34 ዓ.ም ክርስትናን ቀድማ የተቀበለች መሆኗ የታወቀ ነው። የተቀበለችውም በጅሮንድ (በጃንደረባው አማካኝነት) ነው። እርሱም ከፊሊጶስ የተማረውን የክርስትና ትምህርት ለወገኖቹ አስምቷል። የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ "ጃንደረባው ለወገኖቹ ለኢትዮጵያ ሰዎች ሐዋርያ ሆነ" እንዳለ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሐዋርያትን ጉባኤያትና (ኒቂያ፣ ቁስጥንጥንያ ኤፌሶን) ውሳኔዎቻቸውን ትቀበላለች። ሌሎች ጉባኤዎችን አትቀበልም። የታቦታትን (የጽላትን)፣ የስዕልን ክብር፣ የቅዱሳንን በአጸደ ሥጋና ነፍስ ማማለድ ታምናለች ታስተምራለች።

- **የሶርያ (የአንፆኪያ) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ**

በቅዱስ ጴጥሮስ እና በእነ ቅዱስ አግናጥዮስ  በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የተመሰረተችው የሶርያ (ያዕቆባዊት) ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከአርመንና ከሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ (አርንታል) አብያተ ክርስቲያናት ጋር ቦሦስቱ ጉባኤያት (በኒቂያ፣ በቁስንጥንጥንያና በኤፌሶን) የትምህርተ ሃይማኖት ውሳኔዎች ታምናለች።

በኒቂያ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ የአርዮስን የክህደት ትምህርት በጥብቅ የተቃወመው ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ የአንጾኪያ ጳጳስ ነው። የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ እስክንድር ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ለሚነሱት መናፍቃን መልስ ስትሰጥ የቆየች ናት።

- **የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ**

የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስንል በደቡብ ህንድ የሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ (የማላባር፣የኬሬላ) ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ ማለት ነው። ሐዋርያት ዕጣ ሲጣጣሉ ለቶማስ የደረሰችው ሕንድ እንደሆነች መሥራቹም ሐዋርያው ቶማስ እንደሆነ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች።

የሕንድ ቤተክርስቲያን በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፋርስ ግዛት ውስጥ በነበረች የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ተጽንዖ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሕንድን በቅኝ ግዛት በያዟት የካቶሊክ እምነት አራማጅ በነበሩት በፖርቹጋሎች ኋላም በደቾች ተፅንኦ ከዚያም በኋላ የእንግሊዝን መንግስት ድጋፍ ባገኘችው በሶርያ ቤተክርስቲያን ተፅእኖ ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ራሷን በራሷ የመምራት መብትን ተገፋ ከቆየች በኋላ በ1912 ዓ.ም በሶርያ ቤተክርስቲያን ሥር ከመተዳደር ወጥታ ጥንት የነበሩትን የኦቶኖሞስ (ረስን በራስ የማስተዳደር) ሥልጣን እንደገና አቋቋማ ነበር።

- **የአርመን (ጎርጎርዮሳዊት) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ**

አንዳንድ የቤተክርስቲያን ፀሐፊዎች አርመን ውስጥ ክርስትና የተጀመረው በሐዋርያው ታዴዎስና በርተሎሜዎስ በ43 ዓ.ም እንደሆነ የመጀመሪያውም ፓትሪያርክ ታዴዎስ ነበር ሲሉ አብዛዎቹ ግን አርጤኖች ቀደም ሲል ላበረከተው የማስተማር (የስብከት) አገልግሎት በንጉሡ፣ በካህናቱና በሕዝቡ ፈቃድ ቀጶዶቂያ በምትገኝ ቂሣርያ ውስጥ ከሌዎንዲዮስ ዘቂሳርያ በ301 ዓ.ም የጵጵስና ማዕረግ በተቀበለው በቅዱስ ጎርጎሪዮስ ከሳቴ ብርሃን ስብከት የክርስትናን እምነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀበለች ይላሉ።

ታላቁ የቤተክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊ አውሳብየስ ዘቂሳርያ ደግሞ ከጎርጎሪዮስ ከሳቴ ብርሃን ቀደም ሲል ክርስትና አርመን ውስጥ ተሰብኮ እንደነበር በታሪክ መጽሐፉ ፅፏል።

## ምዕራፍ ስድስት

## የፕሮቴስታንቲዝም መነሻና ዓለም አቀፋዊ ገፅታው

በዚህ ክፍል የፕሮቴስታንትን አነሳስ፣ አከፋፈል ከ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ያለውን ሲሆን በተጨማሪም ከፕሮቴስታንት ዓለም የወጡትን የፕሮቴስታንት ውላጆች በአጭሩ እንመለከታለን።

### የፕሮቴስታንት መነሻ

ፕሮቴስታንቲዝም በስፋት መንቀሳቀስ የጀመረው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሉተር አስተምህሮ መሠረት ሲሆን አስቀድሞ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ብዙ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተለዩት ፕሮቴስታንት በእምነትና (በዶግማና ደክትሪን) ፣በአስተዳደር ትምህርቶች ባለመስማማት የተመሰረተ የእምነት ድርጅት ነው።

ለፕሮቴስታንቲዝም እምነት መነሻ የሆነው በካቶሊክ የሃይማኖት ድርጅት ይኖሩ የነበሩት ጆን ካልቪን፣ አልቢጀንሴስ፣ ዋልዴንሴስ፣ ዮሐንስ፣ ዊክሊፍ፣ ዮሐንስ ሑስ፣ ጊሮላም ሳቡናሮላ፣ ማርቲን ሉተር፣ ጆን ካልቢንና ሌሎችም የካቶሊክን

ቤተክርስቲያን የአስተዳደርና የእምነት ትምህርት በመቃወም እርምት ይደረግላቸው የሚል ሀሳብ ካቀረቡ በኋላ በተቃውሞ እየገፉ በመምጣት እንቅስቃሴያቸው ቀጠለ። በዚህም ምክንያት እያንዳንዳቸው ብዙ ተከታዮችን በማፍራት ካቶሊክን የአስተዳደርና የእምነት ትምህርት እንዲራቆት፣ እንዲከፋፈልና በአባላቱ ብዙ ልዩነት እንዲፈጠር አድርገዋል።

ቀደም ብለው የተቃወሙ ንቅናቄያቸውንም በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በጦርነት በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሆነው መከፋፈልን ከጀመሩትና ለፕሮቴስታንቲዝም መስፋፋት ምክንያ ከሆኑት ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

፩. **አልቢጀንሴስ (ንጹሐን)፡-** የተባሉት በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ የብሕትውና ሕይወት የነበራቸው ለፃድቃን ምስልና ስዕል የሚደረገውን የአክብሮት ስግደት፣ የመካነ ንስሐ ( ) ትምሕርት፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንንና ትንሳኤ ሙታንን ይቃወሙ ነበር። በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ ከባድ ውድቀት ሲያደርሱ ለፕሮቴስታንት እምነት ደግሞ የምስራች ነበር።

፪. **ዋልዴንሲስ፡-** ይህ ንቅናቄ ዋልደ በተባለ የልዮን ነጋዴ በደቡብ ፈረንሳይ ውስጥ ተጀመረ። መፅሐፍ ቅዱስን ሴትም ወንድም በራሱ እየተረጎመ ማስተማር ይቻላል በማለት ዓላማውን በዚህ አጸና። መጽሐፍ ቅዱስንም ለሳ በሚመች ሁኔታ ተርጉሞ አቀረበ። እርሱም ተከታቹም በመወገዛቸው የካቶሊክን የእምነት ድርጅት በመቃወም በኢማሊያ የፕሮቴስታንትን እምነት በማስፋፋት የቀደምትነት ቦታ ይዘው ይገኛሉ።

፫. **ዮሐንስ ዊክሊች፡-** የኦክስፎርድ ፕሮፌሰርና የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ካህን ነበር። በካቶሊኮቹ ፓፑ አይሳሳትም የሚለውን አመለካከት በመቃወም የቤተክርስቲያን መሪና ራስ ፍጹም ስጣንም የለውም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይል ነበር። በተጨማሪም የደህንነት መገኛ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፣ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ጌታ ሥጋና ደም ኤለውጥም፣ ወደ ተቀደሱ ገዳማት ለስግደት መሔድ አያስፍግም ወዘተ በማለትና ተቃውሞውን በመቀጠል የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን አውኳት ነበር። ይህም ለፕሮቴስታንቲዝም መመስረትና መስፋፋት አንዱ መንስኤ ነበር።

፬. **ማርቲን ሉተር፡-** በጀርመን አገር አይስሌበን በተባለች ከተማ እንደ አውፓውያን አቆጣጠር በ1483 ዓ.ም ተወለደ። እርሱም የካቶሊክ እምነት ተከታይ ነበር። ማርቲን ሉተር የሉተራንን እንቅስቃሴ እንዲጀምር ያነሳሳው ምክንያት ቢኖረውም የኋላ ኋላ ግን ወደ ፍጹም ስህተት አምርቷል። አንድን ሰው ጻድቅ ብሎ መሴም ኃጢአት እንደሆነ፣ አተቃላይ የጾምን፣ የጸሎትን፣ የክህነትን፣ የቁርባንን፣ የምልጃን ሥርዓት እንዲሁም ትውፊት አይቀበልም። ለአማኞች ብቸኛ ባለስልታን መጽሐፍ ቁዱስ እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም በማለት አተቃላይ የቤተክርስቲያንን ሥርዓት ኤቀበልም። በእርሱ መሪነት የተመሰረተው የፕሮተቴስታንት እምነት ሰሙ እንደሚተቁመን ተቃውሞ ስለሆነ ቤተክርስቲያን ጥገናዊ ለውጥ ያስፈልጋታል በማለት በሐዋርያት መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ወጥቶ ብዙ ነገሮችን ነቅፏል። በ1546 ዓ.ም በሞት ተለይቷል።

፭. **ጆን ካልቪን፡-** በፈረንሳይ ጀገር የተወለደው ካልቪን በ1534 የተመሰረተውን የፕሮቴስታንት እምነት ከሉተር ቀትሎ የተቀበለ ሰው ነው።ፖለቲከኛው ካልቪን በሲውዘርላንድ ከሀገሪቱ ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር ጉቦ በመስጠት እምነቱን አልቀበለው ሲሉ ሰዎችን ይገድል ያስገድል ነበር። ይህንም ያዩ ሰዎች ሁሉ ከሞት ለመዳን የፕሮቴስታንት እምነቱን ይቀበሉ ነበር። በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች የካልቪንን የክህደት ትምህርት መነሻ በማድረግ እስካሁን ድረስ የክርስቶስን ሥጋና ደም መታሰቢያ ነው ሲሉ ይሰማሉ።

**፮.፪. የፕሮቴስታንት መከፋፈል**

ከላይ እንደተገለጹ የፕሮቴስታንቲዝም እንቅስቃሴ በዋናነት በእነ ማርቲን ሉተር አስተምህሮ መሰረት በገሀድ የተጠናከረ ቢሆንም ከዚህ ሁሉ መነሻ የሆኑት ቀደም ሲል በ14ኛው መ.ክ.ዘ ጀምሮ በካቶሊክ ቤተክርስቲያን እምነት ይፈጠር የነበረው ተቃውሞና የብዙ ሰዎች ትግል ነበር።

ከቃሉ እንደምንረዳው ፕሮቴስታንት /Protestant/ ማለት ተቃውሞ ወይም ፕሮቴስት /Protest/ መቃወም ማለት ነው።

ምንም እንኳ በየጊዜው በግልም ይሁን በማኅበር በሳይንሱም ይሁን በፖለቲካው ምክንያት የሚከፋፈል ቢሆንም በዚህ ሃይማኖት ደርጅት ውስጥ ሦስት የተለያዩ አመለካከቶችና የእምነት ልነቶችን ብቻ ለምሳሌ ያህል እነዚህንም እንደሚከተለው እንመለከታለን።

፮.፪.፩. **ወንጌላውያን** / Evangelical/

ይህ የወንጌላውያን እምነት ድርጅት በአስበርግ ከተሰተው የሉተር ሃይማት መግለጫ መካከል በልሳን መናገር፣ በመንፈስ መሙላትም መተጨማሪም የአዲሱ የጴንጤቆስቴ እንቅስቃሴን በጥብቅ ይቃወማል። ስለሆነም የራሱን ድርጅት ለማስፋትና ለማጠናከር ከፕሮቴስታንቱ የእምነት ዓለም ተለይቶ ሁሉን ችሎ ተከፍሏል።

፮.፪.፪. **መጥምቃውያን** /Anabaptists/

በ16ኛው መ.ክ.ዘ ተነሱት አናባፕቲስቶች /ዳግሞ አጥማቂዎች/ ከሌላ የክርስትና እምነት ወደ ድርጅታችው ሰበኩትንና የወሰዱትን ክርስቲያን ሁሉ እንደ ገና /ዳግም ጥምቀት/ ያጠምቃሉ። ለዚህም ነው ወንጌላውን የሚቀበሉትን የሕጻናት

ጥምቀት የማቀበሉት።
እነዚህ የእምነት ድርጅቶች በመንፈስ ቅዱስ መተበቅ ሳይሆን በመንፈስ መሞላትን በአፅንኦት ይቀበላሉ። በመንፈስ መሞላትን መናገር አማኙ ለመዳኑ ማረጋገጫ ነውም ይላሉ።
በካቶሊክ ቤተክርስቲያን በጥብቅ ሚያወግዙት አናባፕቲስቶች በብዙ ክፍል ተከፋፈሉ በመሆናቸው የሚያምኑትም ሚያስተምሪትም የተለያየ ነው። በመካከላቸውም በየጊዜው ጥላቻና መከፋፈል ሚበዛው ለዚህ ነው። በዚህም ምክንያት በየጊዜው ሲከፋፈሉና ሲለያ ይታያሉ።
፮.፪.፫. **አዲሱ ጴንጤቆስቴ እምነት** /New Pentecostal faith/
ይህ ካርማቲክ የተሰኘው አዲሱ ጴንጤቆስጤ እምነት ከፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅቶች አንዱ ነው። ከርቲማኮች /አዲሱ የጴንጤቆስጤ እምነት/ ድህነት ኃጢአት አይደለም፣ ጻድቅም ድህነት ብቻ አይደለም፣ ባለጠግነት ኃጢዓት፣ ብልጽግና ጻድቅ አይደለም ይላሉ። በተጨማሪም በመንፈስ መሞላትና መናገር፣ ተሞልቶም በየቦታው እርቃንን መዞር፣ ከመጠን በላይ ተንከትክቶ መሳቅ /Laughing with Spirit/፣ አካባቢን ማወቅ፣ ለክርስቶስ መሳሳም ይገባል በማለትም ያገኙትን ሁሉ የሚስሙ ናቸው። በመንፈስ መዳሰስ /Pancing with spirit/ ይገባል እሉ ዓለም አትብቆ የሚወደውን ለሥጋ ሕይወት የሚስማማውን የዳንስ ሕይወት በመርሳት የተያያዙት በጭፈራ ሰፈር የሚያውኩ ናቸው።
፮.፫. **የፕሮቴስታንቶቹ ፕሮቴስታንት**
የፕሮቴስታንቶቹ ፕሮቴስታነት ስንል ቀድመው ከነበሩት ወይም ከተመሰረቱት የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅት ባለመስማማት ተለያተው ወትተው ራሳቸውን የእምነት ድርጅት የመሠረቱ ናቸው። እነዚህም በየጊዜው ቁጥራቸው /መከፋፈላቸው/ የሚጨምር ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ ለአብነት ያሕል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።
፮.፫.፩. **የሐዋርት እምነት ድርጅተት**
ቀደም በአሜሪካ ሀገር የተጀመረው በአሁኑ ጊዜ በካሊፎርን እየተስፋፋ የመጣው ኦንሊ ጂሰስ (Only Jesus) በመባል የሚታወቀው ይህ የሐዋርያት እምነት ድርጅት በ1950 ዓ.ም እግዚአብሄር ጉባኤ //The Assenbly of God/ ከተሰኘው የእምነት ድርጅት ተገንትሎ የወታ ጴንጤቆስጤያዊ እምነትን የሚያራምድ የሚያራምድ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ማያምን ሰባልዮሳዊ አመለካከት ያለው ድርጅት ነው።
ትምህርታቸውም እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ በሦስት ዓይነት ቅርጽ ራሱን ገለጠ ይላሉ።
እግዚአብሔር አምላክ በሥጋ ዓይን ሳይታይ መንፈስ ሆኖ ሲኖር በኋላ ዝርው ቃል በሆነ በኢየሱስ ላ አደረ በማለት ተዋሕዶንና የምሥጢረ ሥጋዌን ትምህርት በመንቀፍ የክህደት ቃልን ያስተምራሉ።
ስለመንፈስም ሲናገሩ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ በተባለው ሰው ውስጥ ያደረ እስትንፋስ ነው ብለው ያምናሉ።
ምስጢረ ጥምቀት ዙሪያ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28 ቁጥር 19 ላይ የተጠቀሰውን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መተመቅ እንዲገባ የሚናገረውን የመጽሀፍ ቅዱስ ቃል በመካድ በኢየሱስ ስም ብቻ በማለት ሌሎችንም ያጠምቃሉ።
፮.፫.፪. **ሞርሞኒዝም** /Mermonizm/
የኋለኛው ዘመን ቅዱሳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን /The Church of Jesus Christ of letter day saints/ በመባል የሚታወቀው በአሜሪካን ሀገር 1828 ዓ.ም ገደማ የተመሰረተ የእምነት ድርጅት ነው። ሞርሞኒዝም የሚለውን ስያሜም ሊያገኝ ቻለው መሥራቹ ጆሴፍ ስሚዝ ሁእይ ሲመለከት ሞርሞን የተባለ ሰው አተቃላ ስለ እምነቱና መመሪያዎቹ እንደነገረው ይተረካል። በዚህም ምክንያት የእምነት ድርጅቱ ሁእዩን ባሳየው ሰው በሞርሞን ምክንያት ሞርሞንዝም በመባል ሊተራ ችሏል። የሦስት መለኮት ትምህርትን በማስተማር የሥላሴን ምስጢር የማይቀበለው ሞርሞኒዝም ስለ እግዚአብሔር አብ ሲናገር በአንድ ወቅት ሰው ነበር። ነገር ግን አምላክ ሆነ ሚስቱም እመ ሰማይ ትባላለች። አብም ስጋዊ አካል አለው በማለት የክህደት ትምህርት ያስተምራሉ። እንዲሁም በሌሎች በክሕነትና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያላቸው አመለካከት ፈጽሞ የተለየ የራሳቸውን የስጋ አስተሳሰብ ለማርካት ጥቅማቸውን ሚያሳስዱ ናቸው።
፮.፫.፫. **የይሕዋ ምስክሮች** /Johova Witners/
በ1870 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የተነሳው ቻርልስ ራስል የተባለው ሰው በአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ “ጂሆቫ ዊትነስ” ተባለውን እምነት ድርጅት ፈላስፋ። ቻርልስ ሁስል ለየት ያለ ትምህርት ይዞ ሲነሳም ይህ የሙት ትምህርቱ ግን በ315 ዓ.ም በኒቂያ ላይ ተወገዘው የመቅዶንዮስንና የሌሎችንም መናፍቅቃን ትምህርት አካቶ ያዘ ነው።
የእምነቱ ተከታዮች እንደሚሉት መተሪያ ስማቸውን “የይሐዋ ምስክር” የሚለውን ያገኙት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢሳይያስ 43፥10 እንደ አሜሪካኑ ስታንዳርድ ቨርዥን ( ) አተረጓጎም ነው ብለው ነው። በዚህ ቦታ ላይ “እናንተ የይሐዋ ምስክሮች ናቸው” ይላሉ። እና በኢሳይስ የተነገረልን እኛ ነን ሲሉ ይሰማሉ። በመሰረቱ ይሐዋ የእግዚአብሔር ክቡር ስሙ ቢታወቅም እርሱ ግን

የታላቁ አምለካ ምስክሮች እንዳልሆኑ ሥራዎች ይገኙባቸዋል፡፡
እንደ “ይሆዋ ምስክሮች“ ወይም አርዮሳውያን አባባል ይሐዋ ሁሉን የሚችል አምላክ ሲሆን ለምትፈተረው አዲሲቱ ዓለም ንጉሥ ይሆን ዘንድ የታጨ ነው ይሉታል፡፡ ትምህርታቸውንም በማርዘም ክርስቶስ ማለት የመጀመሪያው መልአክ ሚካኤል ተባለው ነው ብለው ክርስቶስን ሚካኤል ነው ብለው ያምናሉ ያስተምራሉ፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

### የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ ማኅበር(ጉባኤ)

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ ማኅበር ሲባል አብያተ ክርስቲያናት በኅብረት በመሥራት የክርስትናን ትምህርት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም በመግለጽ ለዓለም ህዝብ የሶሻል፤የኢኮኖሚና፤ የፖሎቲካ መሻሻልን ለማበርከት **ሕይወትና ሥራ** የሚለውን የተቀደሰ ተግባር ለማስኬድ አንድ ላይ እየተወያዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስብሰባ ነው፡፡
ይህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ጉባኤ የተመሰረተው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ቀድሞ ቤተክርስቲያን ስትመሰረት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይኖር ኢየሱስ ክርስቶስም፤ ቅዱሳን ሐዋርያት ሌሎችም ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት አመሰራረቷን ዓላማዋን አጠቃላይ ሁኔታ በስፋት አስተምረው ነበር፡፡ ቢያስተምሩም ቅሉ ከጊዜ በኋላ በክርስቲያኖች መካከል በየወቅቱ መለያየት ይፈጠር ነበር፡፡

- **የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ጉባኤ ዓላማ፡**
  - የሃይማኖት ጦርነት እንዳይኖር
  - በክርስቲያኖች መካከል የወንድማማችነት ስሜት ለመፍጠር
  - ችግሮችን በጋራ ለመፍታት
  - እርዳት የሚያስፈልጋቸውን በአንድነት ሆኖ ለመርዳት
- **የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ጉባኤ አስፈላጊነት**

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ጉባኤ ጠቀሜታው የኅብረተሰቡን ሰላም ነጻነትና እኩልነት ለማስጠበቅ ወይም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን የሰዎችንም ሥጋዊ ፍላጎትም እንዲሟላ ጥረት ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም

- የእጎለ ማውታ ትምህርት ቤቶች
- የሽማግሌዎች ጡረታ ቤቶች
- የድኩማን መርጃዎች
- የህሙማን ሆስፒታሎች በብዛት እንዲቋቋሙ ይረዳል፡፡

### የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ጉባኤ ጽ/ቤት

በ1ሺ48 እ.ኤ.አ በሆላንድ ሀገር አምስተርዳም በተባለው ከተማ በፕሮቴስታንቶችና በኦርቶዶክሳውያን አማካኝነት ተመስርቶ ዋና ጽ/ቤቱን ጀኔቫ አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከመስራች አባላት አንዷ ናት፡፡
አጠቃላይ ማኅበሩ ከ304 በላይ አብያተ ክርስቲያናትን (ሀገራትን) ያቀፈ ሲሆን በቋሚ አባልነት ያሉ ከመቶ በላይ አብያተ ክርስቲያናት (ሀገራት) ሲሆኑ የክርስቲያኑ (የአባላቱ)ቁጥር ከ አራት መቶ ሚሊዮን በላይ ነው፡፡ ይህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ ማኅበር የሚመራው በሰባት ዓመት አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ጠቅላላ ጉባኤና በዓመት አንድ ጊዜ በሚሰበሰብ ማዕላዊ ኮሚቴ ውሳኔ በአሁኑ ጊዜ በዓመት የሚሰጠው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ብዛት 134 ሲሆን ከዚህ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ወንበር አላት  ጠቅላላ ጉባኤው በ 7 ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል እስከ አሁን ድረስ ስድስት ጠቅላላ ጉባኤዎች ተካሂደዋል፡፡ እነርሱም እ.ኤ.አ

- በ1918 ዓ.ም አመስተርዳም (ሆላንድ)
- በ1954 ዓ.ም ኢቫንስተን (አሜሪካ)

- በ1961 ዓ.ም ኒውደልሂ (ሕንድ)
- በ1966 ዓ.ም ኤፕሳላ (ስዊድን)
- በ1975 ዓ.ም ናይሮቢ (ኬንያ)
- በ1983 ዓ.ም ባንኮቨር (ካናዳ) ናቸው።

ለአብያተ ክርስቲያናት አንድነት አስተዋጾ ከሚያደርጉት ድርጅቶች አንዱ ሰንዴስሞስ የሚባለው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ወጣቶች ማኅበር ነው።

**የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ጉባኤ**

በአፍሪካ አህጉር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አሰባስቦ የያዘው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው በኩል ለአፍሪካ ሕዝብ ልታበረክት የሚገባትን ድርሻ የሚያስተባብር ጉባኤ ነው። የዚህ ጉባኤ ዋና ጽ/ቤት የሚገኘው በናይሮቢ ኬንያ ዋና ከተማ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ጉባኤ መሥራችና ቋሚ አባል ናት።

በአብያተ ክርስቲያናት ስም የተቋቋሙ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ስደተኞችን በመርዳት፤ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን በስፈራ ጣቢያ በማስፈር በመሰረተ ትምህርት ዘመቻ በመሳተፍ ዘረኝነትና እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን በመቃወም ፀረ ሰላም ድርጊትን በማውገዝ በጠቅላላው ለሰው ልጅ ደኅንነት ከቆሙ ወገኖች ጋር በመሰለፍ ብዙ መልካም አስተዋጽኦዎችን ያደርጋሉ።